# አዋጅ ቁጥር………../2016

## በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀል የደህንነት ስጋት ከመሆኑ በተጨማሪ የፋይናንስ ሥርዓቱ የተረጋጋ፣ ግልጸኝነት ያለው፣ ጤናማና ቀልጣፋ እንዳይሆን የሚያደርግ በመሆኑ፤

ከዚህ ቀደም የነበረው አዋጅ ቁጥር 780/2013 ግልጽነት የጎደለው እና በተግባር ችግር የፈጠረ በመሆኑ ከሌሎች ህጎች ጋር የማይጣጣምና ወቅታዊ ለሆኑ ችግሮች በቂ ምላሽ የማይሰጥ ሆኖ በመገኘቱ በአዲስና በተሟላ የሕግ ማዕቀፍ መተካት በማስፈለጉ፤

በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ለመዋጋት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥረት እየተደረገ በመሆኑና ኢትዮጵያም የዚህ ዓለም አቀፍ ጥረት አካል በመሆኗ እና ይህንን በስራ ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

**ይህ አዋጅ በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር**………../2016 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1) **"የወንጀል ፍሬ"** ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከወንጀል ድርጊት የተገኘ ማንኛውም ንብረት ሲሆን ይህንኑ ንብረት መሰረት አድርጎ የተገኘ ገቢ ወይም ትርፍ፣ ለወንጀል መፈጸሚያነት ከዋለ ንብረት የሚገኝ ገቢ ወይም ትርፍን ይጨምራል፤

2) "**አመንጭ ወንጀል**" ማለት በአይነት ሲገመት ወይም በጥሬ ገንዘብ ከአምስት መቶ ሺህ ብር በላይ የሚያመነጭ ማንኛውም ወንጀል ወይም የገንዘብ መጠኑን ከግምት ሳያስገባ በአባሪ አንድ የተዘረዘሩ የወንጀል አይነቶችን ይጨምራል፡፡

3) **"ንብረት"** ወይም **"ገንዘብ"** በተለዋዋጭ የሚያገለግሉ ቃሎች ሲሆኑ ይህም ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለው ወይም የሌለው ሃብት ሲሆን በሃብቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም መኖሩን የሚያረጋግጥ እንደ ባንክ ክሬዲት፣ ትራቭለር ቼክ፣ ዲጂታል ገንዘብ፣ የክፍያ ትዕዛዝ፣ አክሲዮን ወይም ቦንድ የመሰለ ማንኛውንም ሰነድ እና ከሃብቱ የተገኘን ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ ወይም ሌላ ገቢን ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅምን ይጨምራል፡፡

4) **"ምናባዊ ንብረት"** ማለት በዲጂታል መንገድ ለመገበያየት፣ ለማስተላልፍ ወይም ለኢንቨስትመንት ክፍያ ሊያገልግለ የሚችል ሲሆን በዲጊታል የሚወከሉ የመገበያያ ገንዘብን፣ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች እና ሌሎች ተላላፊ የሆኑ የክፍያ ሰነዶችን አይጨምርም።

5) "**የሽብርተኝነት ድርጊት**" ማለት

ሀ. በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የተፈጸመ እ.ኤ.አ. በ1999 ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል በወጣው ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን አባሪ ከሆኑት ስምምነቶች በአንዱ የተፈጻሚነት ወሰንና ትርጓሜዎች የሚሸፈን ድርጊት፤

ለ. የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ 1176/2012 ላይ የተደነገገውን የሽብርተኝነት ድርጊት ትርጉምን ይጨምራል፡፡

6) "**ሽብርተኛ**" ማለት፣ በዚህ አዋጅ እና የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ 1176/2012 ላይ የተደነገገውን የሽብርተኝነት ድርጊት

የፈፀመ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የሚገኝ ማንኛውም ግለሰብ ግለሰብ ነው፡፡

7) "**የሽብርተኛ ድርጅት**" ማለት፣

ሀ. በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በሌላ ቦታ የሚገኝ ወይም የሚንቀሳቀስ ሆኖ፣

1. በማንኛውም መንገድ፣ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ፣ ሕግን በመጣስና በራሱ ፈቃድ የሽብርተኝነት ድርጊት የሚፈጽም ወይም ለመፈጸም የሚሞክር
2. በሽብርተኝነት ድርጊት በአባሪነት የሚሳተፍ፣
3. ሌሎች ሰዎች በሽብርተኝነት ድርጊት እንዲሳተፉ የሚያደራጅ ወይም አመራር የሚሰጥ
4. ሽብርተኝነትን እንዲያስፋፋ በመፈለግ ወይም ቡድኑ የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም ማሰቡን እያወቀ ለጋራ አላማ በቡድን የተሰባሰቡ ሰዎች ለሚፈጽሙት የሽብርተኝነት ድርጊት አስተዋፆ የሚያደርግ፣

ማንኛውም ቡድን ወይም

ለ. የሽብር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1176/2012 ድንጋጌዎች መሰረት በሽብርተኝነት የተሰየመ ድርጅት ነው፡፡

8) "**የፋይናንስ ተቋም**" ማለት ባንክ፣ መድን ሰጪ ኩባንያ፣ አነስተኛ የፋይናንስ ተቋም፣ የካፒታል ዕቃ ፋይናንስ ኩባንያ፣ የጠለፋ መድን ሰጪ፣ አነስተኛ መድን ሰጪ፣ የፖስታ ቁጠባ ድርጅት፣ የሃዋላ ድርጅት፣ በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ወይም በብሄራዊ ባንክ የሚወሰን ሌላ ተመሳሳይ ተቋም ነው፡፡

9) "**ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች**" ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ. የሪል እስቴት አልሚዎች፣ የሪል እስቴት ወኪሎች፣ ደላሎች፤

ለ. የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶች ነጋዴዎች፤

ሐ. የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች

መ. የሚከተለውን ለደንበኞቻቸው የሚያዘጋጁ፣ የሚፈጽሙ ወይም የሚያከናውኑ ጠበቆችን እና ራሳቸውን ችለው የሚሰሩ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች፡-

1. ሪል ስቴት መግዛትና መሸጥ፤

2. የደንበኛውን ገንዘብ፣ የገንዘብ ሰነዶችና ሃብት ማስተዳደር፤

3. ኩባንያ ለማቋቋምና ለማካሄድ ወይም ለመምራት የሚደረጉ መዋጮዎችን ማደራጀት

4. የባንክ፣ የቁጠባ ወይም የገንዘብ ሰነድ ሂሳቦችን ማስተዳደር ወይም

5. በሕግ የሰውነት መብት የሚኖራቸውን አካላት መመስረት፣ ማካሄድ ወይም መምራትና የንግድ ተቋማትን መግዛትና መሸጥ፣

ረ. ራሳቸውን ችለው የሚሰሩ የሂሳብ ባለሙያዎች

ሰ. በአገልግሎቱ የሚሰየሙ ሌሎች የንግድና የሙያ ሥራዎች

10) "**ሪፖርት አድራጊ ተቋም**" ማለት በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል፡፡

11) "**ለፖለቲካ ተጽኖ የተጋለጠ ሰው**" ማለት በማናቸውም አገር ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሃላፊነት የተሰጠው ወይም ተሰጥቶት የነበረ ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ሲሆን የዚህን ሰው ቤተሰብ አባል ወይም ከዚሁ ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው ይጨምራል፣

12) "**በቁጥጥር ስር የሚደረግ ማስተላለፍ**" ማለት የወንጀል ድርጊትን ለመመርመርና የድርጊቱን ተሳታፊዎች ለመለየት ዓላማ፣ የወንጀል ፍሬን ወይም ህገወጥ የሆነን ወይም የሚጠረጠር ሌላ ጭነትን ወይም ጥሬ ገንዘብን አግባብ ባላቸው ባለስልጣናት እውቅናና ቁጥጥር ስር ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲዘዋወር፣ ከኢትዮጵያ

እንዲወጣ፣ የኢትዮጵያን ግዛት አቋርጦ እንዲያልፍ ወይም ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ የመፍቀድ ስልት ነው፤

13)"**በሽፋን ስር የሚደረግ ምርመራ**" ማለት ምርመራውን የሚያከናውነው አካል በበላይ ሃላፊው አቅጣጫ ሰጭነት እና ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው ፈቃድ መሰረት በጊዜያዊነት ማንነቱ እንዳይታወቅ በማድረግ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ እና ሽብርተኝነት በገንዘብ መርዳት ወንጀልን፣ የአመንጪ መንጀልን፣ የወንጀሉን ተሳታፊዎች፣ የወንጀሉን ፍሬ ወይም ሌሎች ማስረጃዎች የሚሰበሰብበት የምርመራ ዘዴ ነው፡፡

14)"**የወንጀል መፈጸሚያ**" ማለት በማንኛውም መንገድና በሙሉ ወይም በከፊል በዚህ አዋጅ የተደነገገ ወንጀል ወይም አመንጭ ወንጀል ለመፈጸም የዋለ ወይም እንዲውል የታቀደ ማንኛውም ንብረት ነው፡፡

15) "**የተደራጁ የወንጀለኞች ቡድን**" ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የገንዘብ ወይም የሌላ ቁሳዊ ጥቅም በማግኘት አላማ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ከባድ ወንጀሎችን ለመፈጸም የተሰባሰቡና ተቀናጅተው የሚንቀሳቀሱ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የያዘና ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የተደራጀ ቡድን ነው፤

16) "**ኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ**" ማለት ላኪ በሆነው ሰውና በፋይናንስ ተቋም አማካይነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚፈጸም በሌላ የፋይናንስ ተቋም ዘንድ ቀርቦ ክፍያውን ለሚቀበል ሰው ገንዘብ ማስተላለፍ ነው፤

17) "**መዝገብ**" **ወይም** "**ሰነድ**" ማለት ማንኛውንም አይነት መረጃ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፣

ሀ. ጽሁፍ የሰፈረበት ማንኛውም ነገር፤

ለ. ሊተረጉመው ለሚችል ሰው መልዕክት የሚያስተላልፍ በማንኛውም ነገር ላይ ያለን ጭረት፣ ቁጥር፣ ምልክት ወይም ብስ፣

ሐ. በሌላ ነገር እገዛ ወይም ያለ እገዛ ድምጽ፣ ምስል ወይም ጽሁፍ ሊያወጣ ወይም ሊያሳይ የሚችልን ማናቸውም ነገር፤

መ. ካርታን፣ ፕላንን፣ ስዕልን፣ ፎቶን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገርን፤

ሠ. የኤሌክትሮኒክ ሰነዶችን፤

ረ. በሰው፣ በኮምፒውተር ወይም በሌላ መሳሪያ መነበብና መረዳት የሚችል መረጃ የተመዘገበበትን ወይም ምልክት የተደረገበትን ማናቸውም ነገር፤

ሰ. በኮምፒውተር ውስጥ፣ በዲስክ ወይም በካሴት ወይም በማይክሮ ፊልም የተያዘ ወይም በማናቸውም መካኒካል ወይም ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ የተያዘ ማናቸውም መረጃ፤

18)“**አገልግሎት**” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 490/2014 የተቋቋመው የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ነው፤

19)“**አግባብ ያለው ባለስልጣን**” ማለት አገልግሎቱ፣ የብሄራዊ መረጃና ደህንነት አግልግሎት፣ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ ፖሊስ፣ የፍትህ ሚኒስተር ወይም የምርመራ ስራን በሃላፊነት የሚያከናውን አካል፣ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ጉምሩክ ኮሚሽን፣ እነዚህ ተቋማትን ተክተው የሚሰሩ የክልል ተቋማት ወይም የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ነው፤

20)“**የጥርጣሬ ግብይት**” ማለት ከታወቀው የደንበኛው የንግድ ወይም የግል እንቅስቃሴዎች ጋር ወይም ከዚያ ዓይነቱ ሂሳብ ወይም የንግድ ግንኙነት መደበኛ አሰራር ጋር አብሮ የማይሄድ፣ ውስብስብ፣ ያልተለመደ ግብይት፣ የግብይት አካሄድ ወይም አገልግሎቱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚካተት የጥርጣሬ ግብይት ነው፤

21)“**መገበያያ ገንዘብ**” ማለት የኢትዮጵያ ወይም የማናቸውም አገር የወረቀት ወይም የሳንቲም መገበያያ ሲሆን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በሌሎች ህጎች በሚወስነው መሰረት ሌሎች መገበያያዎችን ያጠቃልላል፡፡

22)“**ለአምጪው የሚከፈል ተላላፊ የገንዘብ ሰነድ**” ማለት እንደ ቼክ፣ የመንገደኞች ቼክ፣ የተስፋ ሰነድ፣ እና የገንዘብ ክፍያ ትዕዛዝ የመሰለ ለአምጭው የሚከፈል ወይም ያለገደብ በጀርባው ላይ ተፈርሞ የሚተላለፍ፣ ማንነቱ ለማይታወቅ ሰው

እንዲከፈል የታዘዘ ወይም ሰነዱን በመስጠት ብቻ ሊተላለፍ በሚያስችል ማናቸውም ፎርም የታዘዘ የገንዘብ ሰነድ ሲሆን የክፍያ ትዕዛዙ ተፈርሞበት ሳለ የሚከፈለው ሰው ስም ግን ባለመጻፉ ጉድለት ያለበትን የገንዘብ ሰነድ ይጨምራል፤

23)**“ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎት እና ተመሳሳይ ግንኙነት”** ማለት በአንድ አገር ውስጥ ያለ ባንክ ሌላ አገር ውስጥ ላለ ባንክ አግልግሎት መስጠት ወይም በገንዘብ ተቋማት መካከል ለገንዘብ ሰነዶች ግብይት ወይም ለገንዘብ ዝውውር የሚደረግ ተመሳሳይ ግንኙነት ነው፤

24) **“ደንበኛ”** ማለት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

ሀ. የፋይናንስ ግብይት ወይም ሂሳብ የተዘጋጀለት፣ የተከፈተለት ወይም የተፈጸመለት ሰው፤

ለ. የፋይናንስ ግብይት ወይም የሂሳብ ፈራሚ የሆነ ሰው፤

ሐ. ሂሳብ የተከፈተለት ወይም በፋይናንስ ግብይት መብት ወይም ግዴታ የተሰጠው ወይም የተላለፈለት ሰው፤

መ. የፋይናንስ ግብይት እንዲፈጸም ወይም ሂሳቡን እንዲቆጣጠር ሥልጣን የተሰጠው ሰው፤

ሠ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከፊደል ተራ ሀ እስከ መ ከተገለጹት ድርጊቶች መካከል አንዱን ለመፈጸም የሚሞክርን ሰው፤

ረ. ፋይናንስ ነክ ካልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎችን ከሚያከናውኑ አካላት ጋር የንግድ ወይም የስራ ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው፤

ሰ. በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ማንኛውም ሰው፤

25)**“ተጠቃሚ”** ማለት ጥቅምን ወይም ትርፍን የሚያገኝ ወይም ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረትን እንዲቀበል የተሰየመ ሰው ነው፤

26)**"ተጠቃሚ የሚሆን ባለቤት"** ማለት ደንበኛን ወይም አንድን ሂሳብ በፍጹም ባለቤትነት የሚይዝ ወይም የሚቆጣጠር ግለሰብ፣ ግብይት በስሙ የሚካሄድለት ሰው ወይም አንድን በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል ወይም ከሕግ የመነጨ አደረጃጀትን ለመቆጣጠር ፍጹም ስልጣን ያለው የተፈጥሮ ሰው ነው፤

27)**"ተቆጣጣሪ ባለስልጣን"** ማለት የፋይናንስ ተቋማትን በሚመለከት የብሄራዊ ባንክ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ፋይናንስ ነክ ያልሆነ የተሰየመ የንግድ ወይም የሙያ ስራ እንዲቆጣጠር በሕግ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል ነው፤

28)**"የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ድርጅት ነው፤

29)**"የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ባለስልጣን"** ማለት በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የሚቆጣጠር አካል ነው፤

30)**"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

31)ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የወንጀል ጥፋቶች እና ቅጣት

### 3. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወንጀል

1) ማንኛዉም ሰዉ ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባዉ፡-

ሀ. የንብረቱን ህገወጥ ምንጭ ለመደበቅ ወይም ለመሸፈን የለወጠ ወይም ያስተላለፈ፤ ወይም አመንጭዉን ወንጀል የፈጸመዉ ሰዉ ከሕግ ተጠያቂነት እንዲያመልጥ ለማድረግ ንብረቱን የለወጠ ወይም ያስተላለፈ እንደሆነ፡

ለ. ንብረቱን፣ የንብረቱን ትክክለኛነት፣ ምንጩን፣ ቦታዉን፣ ዝዉዉሩን ወይም የባለቤትነት መብትን የደበቀ ወይም እንዳይታወቅ ያደረገ እንደሆነ፤

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ(1) እንደተጠበቀ ሆኖ ከአመንጭ ወንጀል ፈጻሚው ውጭ የሆነ ሶስተኛ ወገን ንብረቱ የወንጀል ፍሬ መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ ሲገባው የተረከበ፣ በይዞታ ያደረገ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ፤

በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የንብረቱ መወረስ በዚህ አዋጅ መሰረት እንደተጠበቀ ሆኖ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 500(አምስት መቶ) ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሱትን ወንጀል የሚፈጽምን ሰው ለመርዳት ያደመ፣ የሞከረ፣ የደገፈ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈጸም ያማከረ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የንብረቱ መወረስ በዚህ አዋጅ መሰረት እንደተጠበቀ ሆኖ ከ 5 አመት እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 100 ሺ. (አንድ መቶ ሺ.) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የሚጣል ቅጣት በሚከተሉት ምክንያቶች በመክበድ ከ15 ዓመት አስከ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ 1 (አንድ )ሚሊዮን ብር መቀጮ ሊደርስ ይችላል፡-

ሀ. የተፈጸመዉ አመንጭ ወንጀል በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-2 ከተመለከተዉ በላይ የእስር ቅጣት የሚያስከትል ከሆነ፤

ለ. ወንጀሉ የተፈጸመዉ በንግድ ወይም በስራ ተግባርነት ተይዞ ከሆነ፤

ሐ. የተደራጀ የወንጀል ቡድን ከአላማዎቹ አንዱ አድርጎ የፈጸመዉ ከሆነ፤

መ. ህጋዊ እንዲመስል ተደርጎ የቀረበዉ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ግምት ብር ሃያ ሚሊየን ወይም የሚበልጥ ከሆነ፤ ወይም

ሠ. ወንጀሉ የተፈጸመዉ ሌላ ወንጀል እንዲሰራ ለማመቻቸት ከሆነ፡፡

5) ለዚህ አንቀጽ ድንጋጌ አፈጻጸም ሲባል፡-

ሀ. የተከሳሽ የሀሳብ ክፍል ወይም ወንጀሉን ለመፈጸም የተነሳበት አላማ ከተጨባጭ የሁኔታዎች ክስተት በመነሳት ግምት የሚወሰድበት ይሆናል፤

ለ. የንብረቱ ምንጭ ህገወጥ መሆኑን ለማስረዳት በተከሳሽ ላይ በአመንጭዉ ወንጀል የጥፋተኝነት ፍርድ መሰጠቱ የግድ የሚያስፈልግ አይሆንም፤

ሐ. የአመንጭ ወንጀል ድርጊት ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ የተፈጸመ ቢሆንም ድርጊቱ በኢትዮጵያ ዉስጥ ቢፈጸም ኖሮ ወንጀል ሆኖ ሊያስቀጣ የሚችል ከሆነ እንደ አመንጭ ወንጀል ይቆጠራል፤

መ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወንጀል ለመፈጸም መሞከር፣ መደገፍ፣ ማመቻቸት ወይም ማማከር ወንጀሉ እንደተፈጸመ ተቆጥሮ የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

## 4. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ተቀጽላ ወንጀሎች

1) ማንኛዉም ሰዉ ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት፡-

ሀ. ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የያዘዉ ጥሬ ገንዘብ ወይም ለአምጭዉ የሚከፈሉ የገንዘብ ሰነዶችን ያልገለጸ ወይም የሃሰት ማስረጃ የሰጠ ወይም በባለስልጣኑ ሲጠየቅ ለማሳወቅ ፈቃደኛ ካልሆነ ፤

ለ. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ድንጋጌ በመተላለፍ፡-

1. በተመዘገበበት የዉጭ አገር በአካል ከማይገኝ የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብሰብ ዉስጥ ከማይካተት ባንክ ጋር፤ ወይም
2. ሂሳቦቹን በተመዘገበበት የዉጭ አገር በአካል የማይገኙና የተጠናከረ የጋራ አመራር እና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ዉስጥ የማይካተት ባንክ እንዲጠቀምባቸዉ ከሚፈቅድ የፋይናንስ ተቋም ጋር፤

የንግድ ግንኙነት ከመሰረተ ወይም የነበረዉን የንግድ ግንኙነት ካስቀጠለ፤

ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 በተደነገገዉ መሰረት በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጣቸዉን አካላት መሰረታዊና ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለቤቶቻቸዉንና የአመራር

መዋቅራቸዉን የሚመለከት የተሟላ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎች ያልያዘ እንደሆነ፤

መ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ፣15 እና አንቀጽ 16 መሰረት የደንበኞችን ማንነት የማጣራት እና የስጋት መቀነሻ እርምጃዎችን ያልወሰደ እንደሆነ፤

ሠ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሰረት የክትትል እርምጃዎችን ያልወሰደ እንደሆነ፤

ረ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18 መሰረት መዝገብ ያልያዘ ወይም መዝገብ እንዲወድም ወይም እንዲወገድ ያደረገ እንደሆነ፤

ሰ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19 በተደነገገዉ መሰረት የዉስጥ የቁጥጥር ፕሮግራም ተግባራዊ ያላደረገ እንደሆነ፤

ሸ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12፣ 18 ወይም አንቀጽ 23 መሰረት አግባብ ባላቸዉ ባለስልጣኖች ሲጠየቅ በወቅቱ መረጃ ያልሰጠ ወይም መዝገብ ያላሳየ እንደሆነ፤

ቀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 መሰረት ጥርጣሬዎችን በሚመለከት ለአገልግሎቱ ሪፖረት ያላቀረበ እንደሆነ፤

በ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25 መሰረት የጥሬ ገንዘብ ግብይቶችን በሚመለከት ለአገልግሎቱ ሪፖረት ያላቀረበ እንደሆነ፤

ተ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 መሰረት ሲጠየቅ ግብይት ከመፈጸም ለመቆጠብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ፤ወይም

ቸ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 እና 30 የተደነገገዉን በመተላለፍ መረጃ ለደንበኛ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ሰዉ አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሶስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና ከብር 100ሺ (አንድ መቶ ሺህ) እሰከ 500ሺ (አምስት መቶ ሺህ) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰዉ ማንኛዉም ተቀጽላ ወንጀል ጥፋተኛ የሆነ ሰዉ ከእስራቱ እና ከገንዘብ ቅጣቱ በተጨማሪ ወንጀሉን ለመፈጸም እድል

የፈጠረለትን የንግድ ወይም የሙያ ስራ ለዘለቄታዉ ወይም ከአምስት ዓመት ለማያንስ ጊዜ እንዳይሰራ ሊታገድ ይችላል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚጣሉ ቅጣቶች ተቆጣጣሪ ባለስልጣኖች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 መሰረት ሊወስዱ የሚችሏቸዉ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን አያስቀሩም፡፡

5. ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት

1) ማንኛዉም ሰዉ፡-

ሀ. ገንዘቡ በሙሉ ወይም በከፊል፡-

1. የሽብርተኝነት ድርጊት ለመፈጸም፤
2. ለአሸባሪ መጠቀሚያ፤ ወይም
3. ለሽብርተኛ ድርጅት መጠቀሚያ፤

እንዲዉል በማሰብ ወይም እንደሚዉል እያወቀ በማንኛዉም መንገድ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገዛ ፈቃዱ ገንዘብ የሰጠ ወይም የሰበሰበ ወይም ገንዘብ ለመስጠትም ሆነ ለመሰብሰብ የሞከረ እንደሆነ፤

ለ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተዉን ወንጀል በመፈጸም በአባሪነት የተሳተፈ እንደሆነ፤

ሐ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተዉን ወንጀል ለማስፈጸም ሌሎችን ያደራጀ ወይም አመራር የሰጠ እንደሆነ፤

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሰረት የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 500 ሺ (አምስት መቶ ሺህ) የማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2) በንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል ተራ ሀ እስከ ሐ የተመለከቱት ወንጀሎች የሚፈጽምን ሰው ለመርዳት ያደመ፣ የሞከረ፣ የደገፈ፣ ያመቻቸ ወይም እንዲፈጸም ያማከረ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ፤ በዚህ አዋጅ መሰረት የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከ5 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50 ሺ (ሀምሳ ሺህ) የማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ  በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት የሚጣል ቅጣት በሚከተሉት ምክንያቶች በመክበድ ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት ጽኑ እስራት እና እስከ ብር 1(አንድ) ሚሊዮን መቀጮ ሊደርስ ይችላል፡፡

ሀ. ወንጀሉ የተፈጸመው በንግድ ወይም በስራ ተግባርነት ተይዞ ከሆነ፤ ወይም

ለ. የተደራጀ የወንጀል ቡድን ከአላማዎቹ አንዱ አድርጎት የፈጸመው ከሆነ፡፡

4) ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወንጀል መሳተፍ፣ ወንጀሉን ለመፈጸም ማደም፣ መሞከር፣ መደገፍ ማመቻቸት ወይም ማማከር ወንጀሉ እንደተፈጸመ ተቆጥሮ የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

## 6. ሌሎች ወንጀሎች

1) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ወይም በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ከተሰጠ ትእዛዝ ጋር በተያያዘ ለሚደረግ ምርመራ ጠቃሚ የሆነ ሰነድ ወይም ቁስ ወደ ሐሰት የለወጠ፣ ያጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ያስወገደ ወይም ወደ ሀሰት ሰነድነት እንዲለወጥ፣ እንዲጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ እንዲወገድ የፈቀደ እንደሆነ፤

2) በአገልግሎቱ ዘንድ የተቀመጠውን መረጃ ሆነ ብሎ ያጠፋ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሚፈለገው ዓላማ እንዳይውል ያደረገ እንደሆነ፤ ወይም

3) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ድርጊት ላይ ምስክር የሆነን ወይም ለመሆን የሚችል ሰውን እንዳይመሰክር የደለለ ወይም ያስፈራራ ወይም በምስክሩ ወይም ከምስክሩ ጋር የቅርብ ግንኙነት ባለው ሰው ላይ የሀይል ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ፤

በሌሎች ህጎች የተቀመጠ ቅጣት ከዚህ የሚበልጥ ካልሆነ በስተቀር ከአምስት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና ከብር 50 ሺ (ሀምሳ ሺህ) እስከ 100 ሺ (አንድ መቶ ሺህ) በሚደርሰ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 7. በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ላይ የሚጣል ቅጣት

1) የመንግስት አካል ያልሆነ ማንኛውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፡-

ሀ. ወክሎት በሚሰራ ወይም በዚሁ አካል ውስጥ የመቆጣጠር ሥልጣን ያለው ግለሰብ በተናጠልም ሆነ ከሚመራው ቡድን ጋር በመሆን ሲሰራ አካሉን በመወከል ወይም ለአካሉ ጥቅም ሲባል በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል የተፈፀመ እንደሆነ ፣ ወይም

ለ. በአካሉ ሀላፊነት ስር የሚሰራን ግለሰብ በሚመለከት ሊደረግ በሚገባው ክትትልና ቁጥጥር መጓደል ምክንያት አካሉን በመወከል ወይም ለአካሉ ጥቅም ሲባል በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀል የተፈፀመ እንደሆነ፤

ግለሰቦቹ በወንጀል ፈፃሚነት ወይም አባሪነት የጥፋተኝነት ፍርድ ቢሰጥባቸውም ባይሰጥባቸውም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ወይም አንቀጽ 6 የተመለከተው የገንዘብ ቅጣት በአስር ተባዝቶ ይፈፀምበታል፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት በወንጀል ተጠያቂ የተደረገ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል፣ በፍርድ ቤት ተጨማሪ ውሳኔ፡-

ሀ. የተወሰኑ የንግድ ስራዎችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለዘለቄታው ወይም ከአምስት ዓመት ለማያንስ ጊዜ እንዳያካሂድ ሊታገድ፤

ለ. ወንጀሉን ለመፈፀም በጥቅም ላይ የዋለውን የስራ ቦታውን ለዘለቄታው ወይም ከአምስት አመት ለማያንስ ጊዜ እንዲዘጋ፤; ወይም

ሐ. እንዲፈርስና ሂሳቡ እንዲጣራ ሊደረግ፤ ይችላል፡፡

3) በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ መሰረት በወንጀል መጠየቁ ወንጀሉን በመፈፀም የተሳተፉ ግለሰቦችን ከተጠያቂነት አያድናቸወም፡፡

8. የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች

በወንጀል ህጉ አንቀፅ 179 የተመለከቱት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው የወንጀሉ ፈፃሚ ለፍትህ አካላት፡-

1) ወንጀሉ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል ወይም ለመቀነስ፣
2) የወንጀሉን ሌሎች ፈፃሚዎች ለመለየት ወይም ለፍርድ ለማቅረብ፣
3) ከወንጀሉ ጋር የተያያዘ ማስረጃ ለማግኘት፣ ወይም
4) የተደራጁ የወንጀለኛ ቡድኖችን ሀብታቸውን ወይም በወንጀል ፍሬነት ያገኙትን ለማሳጣት፣

የሚያስችላቸውንና በሌላ መንገድ ሊያገኙ የማይችሉትን መረጃ የሰጣቸው እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ወይም አንቀጽ 6 የተመለከቱት ቅጣቶች ሊቀነሱለት ይችላሉ፡፡

## ክፍል ሶስት

## በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን ስለመከላከል

9. ድንበር አቋርጦ ስለማጓጓዝ ጥሬ ገንዘብና ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን

1) ማንኛውም ሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ወይም ከኢትዮጵያ ሲወጣ የያዛቸውን ገንዘብ፣ ላምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን በተመለከተ አግባብ ባለው አካል በሚወጣው ሕግ መሰረት ለጉምሩክ ኮሚሽን የማሳወቅ ግዴታ አለበት::

2) በፖስታ ወይም በካርጎ ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጡ ጥሬ ገንዘብ፣ ላምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን ለጉምሩክ ኮሚሽን የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት የሚከናወን የማሳወቅ ሂደት አለምአቀፍ የንግድ ክፍያ ሥርዓቶችን እና የካፒታል እንቅስቃሴ በማያስተጓጉል መርህ የሚከናወን ይሆናል፡፡

4) ለጉምሩክ ኮሚሽን ገንዘብን፣ ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮች ወይም የከበሩ ብረቶችን አስመልክቶ ሀሰተኛ መግለጫ የተሰጠ እንደሆነ ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሰረት መግለጫ ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ ወይም ገንዘቡን፣ የክፍያ ሰነዶችን፣ የከበሩ ድንጋዮችን ወይም የከበሩ ብረቶችን በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል፣ በአመንጭ ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ውጤት ስለመሆናቸው ወይም ወንጀሉን ለመፈጸሚያነት እንደሚውሉ ጥርጣሬ ሲኖር ምንጩን እና ለምን አላማ እንደሚውል ተጨማሪ መረጃ የመጠየቅ እና የመያዝ ስልጣን ይኖረዋል፡፡ ሂደቱም አለምአቀፍ የንግድ ክፍያ ሥርዓቶችን እና የካፒታል እንቅስቃሴ በማያስተጓጉል መርህ የሚከናወን ይሆናል፡፡

5) በጉምሩክ አዋጅ የእቃ ውርስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የተያዘ ገንዘብ፣ የክፍያ ሰነድን፣ የከበረ ብረትና የከበረ ድንጋይ በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

6) የጉምሩክ ኮሚሽን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ከተመለከተው ጥርጣሬ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለአገልግሎቱ ማቅረብ አለበት፡፡

7) የጉምሩክ ኮሚሽን ህገወጥ ጥሬ ገንዘብን እና ለአምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን ድንበር አቋርጦ ስለማጓጓዝ እና በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር አግባብነት ካላቸው ባለስልጣናት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

8) የጉምሩክ ኮሚሽን የሚከተሉትን መረጃዎች አጠናቅሮ ይይዛል፡-

ሀ. የገንዘብ መጠን፣ ላምጭው የሚከፈሉ የክፍያ ሰነዶችን እና የመግለጫ አቅራቢውን ማንነት የሚገልጽ

መረጃን ያካተተ መግለጫዎችን፣

ለ. ሃሰተኛ መግለጫዎችን፣

ሐ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል፣ በአመንጭ ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ጋር የተያያዙ የጥርጣሬ መረጃዎችን።

## 10.ስለድንበር ተሻጋሪ የባንክ ግንኙነት

የፋይናንስ ተቋማት፡-

1) በተመዘገበበት ወይም ፈቃድ ባወጣበት የውጭ አገር በአካል ከማይገኝና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ ከማይካተት ባንክ፤ ወይም

2) በተመዘገበበት ወይም ፈቃድ ባወጣበት የውጭ አገር በአካል የማይገኝና የተጠናከረ የጋራ አመራርና ቁጥጥር ከሚደረግበት የፋይናንስ ተቋማት ስብስብ ውስጥ የማይካተት ባንክ ሂሳቦችን እንዲጠቀምባቸው ከሚፈቀድ የፋይናንስ ተቋም፤

ጋር ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎት ወይም ተመሳሳይ የስራ ግንኙነት ሊመሠርቱ ወይም የነበራቸውን ግንኙነት ሊቀጥሉ አይገባም፡፡

## 11.በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላትን የሚመለከት ግልጽነት

1) በኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋሙ ወይም የተመዘገቡ እና በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት መሰረታዊ ፤እና ተጠቃሚ ስለሚሆኑት ባለቤቶቻቸው፤ ስለአመራር መዋቅራቸው የተሟሉ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃዎች መያዝ አለባቸው፡፡

2) አግባብ ያለው ባለስልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን መረጃዎች ሲጠይቅ በተፋጠነ መንገድ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

## 12.ስጋት ስለመለየት

1) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰልና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን በመከላከልና በመቆጣጠር ዙሪያ ያሉትን ስጋቶች መለየት እና መመዘን በግኝቱ መሰረትም አግባብ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተካሄደው የስጋት ምዘና እና ከዚሁ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ጠቃሚ ማስረጃና መረጃ በፅሁፍ ተመዝግቦና ወቅታዊነቱ ተጠብቆ መያዝና በተፈለገ ጊዜ ለአገልግሎቱ፣ ለፖሊስ፣ ለአቃቤ ሕግና የምርመራ ስራን በሃላፊነት ለሚመራ አካል ተደራሽ መሆን አለበት፡፡

3) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ. አዳዲስ አገልግሎቶችን፣ አገልግሎት መስጫ ዘዴዎችንና አሰራሮችን በስራ ላይ ከማዋል ወይም ለአዲስም ሆነ ነባር አገልግሎቶች አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም ጋር ተያይዞ የሚመጡ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ስጋቶችን መለየት መመዘን እና

ለ. እነዚህን ስጋቶች ለመቆጣጠርና ለመቀነስ ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

## 13.የደንበኛን ማንነት ስለማጣራት

1) የፋይናንስ ተቋም ወይም ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራ፡-

ሀ. ከደንበኛ ጋር የንግድ ግንኙነት ከመመስረቱ ወይም ሂሳብ ከመክፈቱ በፊት፤

ለ. በፋይናንስ ተቋም ዘንድ የባንክ ሂሳብ ከሌለው ወይም ፋይናንስ ነክ ካልሆነው የተሰየሙ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ጋር የሥራ ግንኙነት ከሌለው እና፡-

1. በአንድ ጊዜ ወይም የተያያዙ ሆነው በተለያየ ጊዜ ቢፈጸሙም ሲዳመሩ በአገልግሎቱ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ የሆኑ

ግብይቶችን ለመፈፀም ከሚፈልግ ደንበኛ ጋር ግብይት ከመጀመሩ በፊት ወይም

2. በአገር ውስጥ ወይም ወደ ውጭ በኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ማስተላለፍ ከሚፈልግ ደንበኛ ጋር ግብይት ከመጀመሩ በፊት፤

ሐ. ቀደም ሲል የተወሰደ የደንበኛ መረጃ ትክክለኛ ወይም የተሟላ ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሲፈጠር፤ ወይም

መ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን የሚመለከት ጥርጣሬ ሲኖር፤

የደንበኛን ማንነት ለማወቅ የሚያስችሉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የደንበኞችን ማንነት ለማወቅ የሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

ሀ. የንግድ ግንኙነት አላማና ባህሪ መረዳትና መረጃ ማሰባሰብን፤

ለ. ገለልተኛ የሆኑ አስተማማኝ ምንጮችን፤ ሰነዶችን፤ ዳታዎችንና መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ደንበኛውን መለየትና ማንነቱን ማረጋገጥን፤

ሐ. ተጠቃሚ የሚሆኑትን ባለቤቶች ማንነት መለየትን እና ይህንኑ ለማረጋገጥ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድን፤

መ. ደንበኛን ወክሎ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ከደንበኛው ውክልና የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥና እንዲሁም ማንነቱን መለየትና ማረጋገጥን፤ እና

ሠ. በአገልግሎቱ የሚወሰኑ ሌሎች እርምጃዎች መውሰድን፡፡

3) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች ከደንበኞቻቸው ጋር የሚኖሩዋቸውን እያንዳንዱን የሥራ ግንኙነት ያለማቋረጥ በጥንቃቄ መከታተልና የሚፈጽሟቸው ግብይቶች ስለደንበኞቻቸው ካላቸው

እውቀት፣ ከንግድ ሥራዎቻቸውና ከስጋት ደረጃዎቻቸው እና አስፈላጊ ሲሆን ከገንዘብ ምንጮቻቸው ጋር መጣጣሙን በትኩረት መመርመር አለባቸው፡፡

4) የፋይናንስ ተቋማት ድንበር ተሻጋሪ የባንክ አገልግሎትን እና ተመሳሳይ ግንኙነትን በተመለከተ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ከተደነገጉት እርምጃዎች በተጨማሪ፡-

ሀ. የእያንዳንዱን ተቋም ሃላፊነት በግልጽ መረዳትና መመዝገብ፤

ለ. ግንኙነት የፈጠሩበትን የፋይናንስ ተቋም የሚመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብ እና የሥራ ባህሪያቸውን በተሟላ ሁኔታ መረዳት፤

ሐ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ምርመራ የተካሄደበት መሆን አለመሆኑን ጨምሮ ለህዝብ ይፋ በተደረጉ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ የፋይናንስ ተቋሙን መልካም ስም እና የሚደረግበትን የቁጥጥር ዓይነት መገምገም፤

መ. አዲስ ድንበር ተሻጋሪ የባንክ ግንኙነት ወይም ተመሳሳይ ግንኙነት ከመመሥረቱ በፊት የከፍተኛ አመራር አባላት ፈቃድ እንዲገኝ ማድረግ፤

ሠ. ግንኙነት የፈጠሩበት የፋይናንስ ተቋም በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰልና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀልን ለመከላከል በስራ ላይ ያዋለውን የቁጥጥር ሥርዓት መገምገምና፤ እና

ረ. በባንክ ሂሳብ አማካይነት ክፍያ የሚፈጽም ሲሆን ግንኙነት የፈጠሩበት የፋይናንስ ተቋም የባንክ ሂሳቡ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ደንበኞችን ማንነት ለማጣራት በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 አስከ 3 መሰረት የተደነገጉ እርምጃዎችን መውሰዱን እና በአስተላላፊ ተቋሙ ሲጠየቅም ሁሉንም የደንበኞች ማንነት መረጃዎች ማቅረብ የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፤ አለባቸው፡፡

5) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 4 የተመለከቱትን ጥንቃቄ የማድረግ

ግዴታዎቻቸውን ሊወጡ የማይችሉ ሲሆን የስራ ግንኙነቱን መመስረት፣ የባንክ ሂሳብ መክፈት ወይም ግብይት መፈፀም የለባቸውም፤ የንግድ ግንኙነት መስርተውም ከሆነ ማቋረጥ አለባቸው፡፡ አግባብ ሆኖ ሲገኝም በዚህ አዋጅ መሰረት ለአገልግሎቱ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡

6) የፋይናንስ ተቋማት ባልታወቀ ወይም የፈጠራ መሆኑ በግልጽ በሚታወቅ ስም የባንክ ሂሳብ መክፈት የለባቸውም፡፡

## 14. ማንነትን የመለየት ልዩ ግዴታ

1) የከበሩ ድንጋዮችና የከበሩ ብረቶች ነጋዴዎች በአገልግሎቱ ከተወሰነው መጠን በላይ የሆኑ ክፍያዎችን ሲቀበሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሰረት የደንበኞቻቸውን ማንነት መለየት አለባቸው፡፡

2) የባለሞተር ተሽከርካሪ ነጋዴዎች፣ የሪል ስቴት አልሚዎች፣ ወኪሎችና ደላሎች በሪል ስቴት ግዥና ሻጭ ወይም በተሽከርካሪ ሻያጭ ሲሳተፉ የተዋዋዮችን ማንነት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሰረት መለየት አለባቸው፡፡

## 15. የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የሚመለከቱ ግዴታዎች

1) ሥራቸው የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የሚጨምር የፋይናንስ ተቋማት የላኪውን ሙሉ ስም፣ የባንክ ሂሳብ ቁጥር እና አድራሻ ወይም አድራሻ ከሌለ የዜግነት መታወቂያ ቁጥርን ወይም የትውልድ ዘመንና ቦታን እና ለማስተላለፍ ጥቅም ላይ የዋለውን የተጠቃሚውን የባንክ ቁጥር መውሰድና ማጣራት አለባቸው፡፡ መረጃው በኤሌክትሮኒክ የማስተላለፍ መልዕክቱ ወይም የክፍያ ፎርሙ ውስጥ መካተት አለበት፡፡ የባንክ ሂሳብ ቁጥር በማይኖርበት ጊዜ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፊያው ልዩ ማጣቀሻ ቁጥር እንዲይዝ ይደረጋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት የፋይናንስ ተቋማት በኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ ሂደት በአቀባባይነት የሚሳተፉ ሲሆን እነዚህኑ መረጃዎች መያዝና አብረው ማስተላለፍ አለባቸው፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች፡-

ሀ. የክሬዲት ካርድ ወይም የዴቢት ካርድ ቁጥሩ አብሮ እስከተገለጸ ድረስ በክሬዲት ካርድ ወይም በዴቢት ካርድ አማካኝነት የተፈጸመ ግብይትን ተከትሎ የተደረገ ማስተላለፍን፤ ወይም

ለ. ላኪውና ተቀባዩ ሁለቱም የፋይናንስ ተቋማት ሆነው በመካከላቸው የሚፈጽሙትን የገንዘብ ማስተላለፍ፤

በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

4) የፋይናንስ ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱ መረጃዎችን አሟልቶ ያልያዘ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ ትዕዛዝ ሲያጋጥም የማስተላለፍ ትዕዛዙን ተግባራዊ ማድረግ የለበትም፡፡

5) ድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍ የሚሰጥ ወይም የሚቀበል ማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ላኪውን ወይም ተቀባዩን በሚመለከት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚፈለጉ መረጃዎች የሚጎድሏቸውን በኤሌክትሮኒክ ማስተላለፎች ለመለየት ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድና እንደ ስጋቱ መጠን የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን ለመፈጸም ወይም ለመቀበል፣ ውድቅ ለማድረግ ወይም ለማገድ እና መወሰድ ያለባቸውን የክትትል እርምጃዎች ለመወሰን የሚያስችል ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ አለበት፡፡

6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ያልተሟላ የላኪውን መረጃ የያዘ የድንበር ተሻጋሪ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን የስጋት መጠኑ ዝቅተኛ መሆኑን ወስኖ የተቀበለ የፋይናንስ ተቋም የተጠቃሚውን ማንነት ማጣራት አለበት፡፡

7) በአሰራር የሚፈጠሩ የቴክኒክ ጉድለቶች የአገር ውስጥ የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን አስመልክቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱ የላኪው ወይም የተቀባዩ መረጃዎች እንዳይተላለፉ ያደረጉ እንደሆነ ማስተላለፉን ያስፈጸመው ተቋም ከላኪው ወይም የማስተላለፉን ትዕዛዝ ከሰጠው ተቋም ያገኛቸውን መረጃዎች በሙሉ መዝግቦ መያዝ አለበት፡፡

## 16.የተጠናከሩ ወይም ቀለል ያሉ የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሳሰድ

1) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ሊፈጸም ይችላል የሚል ከፍተኛ ስጋት መኖሩ ሲታወቅ የተጠናከረ የደንበኞችን ማንነት የመለየት እርምጃዎች ወይም ስጋቱ ዝቅተኛ መሆኑ ሲታወቅ ቀለል ያለ የደንበኞችን ማንነት የመለየት እርምጃዎች መውሰድ ይችላሉ፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም የፋይናንስ ተቋማትና የፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ. ውስብስብ የሆኑ ግብይቶችን፣ ባልተለመደ ሁኔታ ከፍተኛ መጠን ያላቸው ግብይቶችን፣ ያልተለመዱ ሥርዓቶችን በመከተል የሚፈጸሙ ግብይቶችን እና በግልጽ ሊታይ የሚችል ኢኮኖሚያዊ ወይም ሌላ ህጋዊ ዓላማ የሌላቸውን ግብይቶች እና

ለ. በዓለም አቀፍ ደረጃ ክትትል እንዲደረግባቸው ጥሪ በቀረበባቸው አገሮች ውስጥ ከሚገኙ ወይም ከነዚሁ አገሮች ከመጡ ሰዎች ጋር የሚደረጉትን የንግድ ግንኙነቶችና ግብይቶች፤

በሚመለከት የተጠናከረ የደንበኞችን ማንነት የመለየትና የክትትል እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው፡፡

3) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች አንድ ደንበኛ ሊሆን የሚችል ወይም ደንበኛ የሆነ ወይም ተጠቃሚ የሚሆን ባለቤት ለፖለቲካ ተጽኖ የተጋለጠ ሰው መሆን አለመሆኑን ለመለየት የሚያስችል አግባብ ያለው የስጋት መቀነሻ ዘዴ በሥራ ላይ ማዋልና እንደዚህ ዓይነት ደንበኛ ሲያጋጥምም፡-

ሀ. ከደንበኛው ጋር የስራ ግንኙት ከመመስረቱ በፊት የከፍተኛ አመራር አባላት ፈቃድ እንዲገኝ ማድረግ፤

ለ. የደንበኛውን የሃብትና የገንዘብ ምንጭ ለማወቅ ተገቢ የሆነውን እርምጃ መውሰድ፤ እና

ሐ. ከደንበኛው ጋር በሚኖራቸው የስራ ግንኙነት የተጠናከረ የማያቋርጥ ክትትል ማድረግ አለባቸው፡፡

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ሀ) የተመለከቱት ግብይቶች መነሻ ምክንያቶችና ዓላማዎች በተቻለ መጠን ምርመራ ተካሂዶባቸዉ የተገኙት መረጃዎች በፅሁፍ ተመዝግበዉ መያዝ አለባቸዉ።

5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሰረት የሚወሰዱ እርምጃዎች ዉጤታማና ከስጋቱ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለባቸዉ፤ አገልግሎቱም እነዚህኑ በተመለከተ የበኩሉን ተጓዳኝ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል።

**17.የመዝገብ አያያዝ**

1) የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 14 እስከ አንቀፅ 17 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት የደንበኞችን ማንነት ከማጣራት እርምጃዎች የተገኙ የትንታኔ ዉጤቶች ጨምሮ የሂሳብ መዝገቦችን እና መጻጻፎችን የንግድ ግንኙነቱ ካበቃበት ቀን አንስቶ ወይም ግብይቱ የተካሄደዉ ወይም የግብይት ሙከራዉ የተደረገዉ  የንግድ ግንኙነት ካልመሰረተ ደንበኛ ጋር ከሆነ ግብይቱ ከተካሄደበት ወይም ከተሞከረበት ቀን አንስቶ፡ እና

ለ. የኤሌክትሮኒክ ማስተላለፍን ጨምሮ የአገር ዉስጥም ሆነ ድንበር ተሻጋሪ፣ የተሞከሩም ሆነ የተፈፀሙ ሁሉንም ግብይቶች የሚመለከቱ የተሟሉና የእያንዳንዱን ግብይት መረጃዎች መልሶ ለማየት የሚያስችሉ ዝርዝሮችን የያዙ መዝገቦችን ግብይቱ ከተፈፀመበት ወይም የግብይት ሙከራዉ ከተደረገበት ቀን አንስቶ ቢያንስ ለአስር አመታት ይዘዉ ማቆየት አለባቸዉ።

2) የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንድ መሰረት የተያዙ መዝገቦች አገልግሎቱ እና ሌሎች

አግባብ ያላቸዉ ባለስልጣናት ሊያዩዋቸዉ እንዲችሉ ዝግጁ ሆነዉ መቀመጣቸዉን ማረጋገጥ አለባቸዉ።

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎች መዝገቦችን ለበለጠ ጊዜ ጠብቆ ስለመያዝ በሌሎች ህጎች የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ተፈፃሚነት አያስቀርም፡፡

## 18.የዉስጥ የመከላከል ፕሮግራሞች

1) የፋይናንስ ተቋማት በዚህ አዋጅ አንቀጽ አስራ ሶስት የተጠቀሱትን ወይም በዚህ አዋጅ አንቀፅ 21 (3) መሰረት በአገልግሎቱ ተለይተዉ የተገለፁትን ስጋቶች ዉጤታማ በሆነ መልኩ ለመቆጣጠር እና ለመቀነስ የሚያስችሉ በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል የዉስጥ ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች መዘርጋትና በስራ ላይ ማዋል እንዲሁም የእነዚህን ፖሊሲዎችና ቁጥጥሮች አተገባበር መከታተልና አስፈላጊ ሲሆንም ማጠናከር አለባቸዉ።

2) በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በስራ ላይ እንዲዉሉ የሚደረጉ ፖሊሲዎች እና ቁጥጥሮች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸዉ፡-

   ሀ. በዚህ አዋጅ መሰረት ተጠቃሚ ባለቤቶችን ማንነት መለየትና ማረጋገጥን ጨምሮ የደንበኞችን ማንነት የመለየትና የማረጋገጥ እርምጃዎችን፣ ግብይት መከታተልን እና የማያቋርጥ የጥንቃቄ እርምጃዎችን አወሳሰድ ሥርዓትን፣

   ለ. የሕግ ማክበርን ተገቢ በሆነ ቡድን ደረጃ የማደራጀት እና የማረጋገጥ አመራር ሥርዓትን፣

   ሐ. ከፍተኛ የብቃት ደረጃን ለማስጠበቅ የሚያስችል የተሟላ የሰራተኞችን ምልመላ ሥርዓትን፣

   መ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር ግንኙነት ሊኖራቸዉ የሚችሉ አጠራጣሪ ግብይቶችንና እንቅስቃሴዎችን ለመለየት የሚያግዙ ስልጠናዎችን ጨምሮ ተከታታይ የሆኑ ስልጠናዎችን ለሃላፊዎችና ለሰራተኞች መስጠት፣

ሠ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) መሰረት የሚደራጅ ቡድን ውስጥ የሚመደቡ ሰራተኞች በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን በተመለከተ ስልጠና የወሰዱ እና ለዚሁም ልዩ የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆን አለባቸው፤

ረ. የደንበኞችን ማንነት ለማጣራትና በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ስጋቶችን ለመቆጣጠር የመረጃ ልዉዉጥ ደህንነትና አጠቃቀምን ጨምሮ መረጃዎችን በፋይናንስ ተቋማት መካከል ለመለዋወጥ የሚያስችል ሥርዓትን፣ እና

ሰ. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወሰዱ እርምጃዎች መከበራቸዉንና ዉጤታማ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችል የዉስጥ ኦዲት ሥርዓትን፡፡

3) የፋይናንስ ተቋም ይህ አዋጅ በተቋሙ መከበሩን የማረጋገጥ ሃላፊነት ያለዉ ኦፊሰር በከፍተኛ አመራር ደረጃ መመደብ አለበት።

4) የፋይናንስ ተቋማት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ መሰረት ያወጧቸዉ ፖሊሲዎች እና የቁጥጥር ሥርዓቶች በዉጭ ያሉ ቅርንጫፎቻቸዉ እና በአብላጫ ባለቤትነት የያዟቸዉን ተቋሞቻቸዉን ጨምሮ በቡድን ደረጃ ተግባራዊ መደረጋቸዉን ማረጋገጥ አለባቸዉ።

5) አገልግሎቱ ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር በተያያዘ የሚኖረዉን የስጋት ተጋላጭነትና የስራዉን ስፋት በማገናዘብ በዚሁ አንቀጽ ለተመለከተዉ ለእያንዳንዱ ግዴታ ምን ዓይነት እርምጃዎች መወሰድ እንደሚገባቸዉ በመመሪያ ይወሰናል።

## 19.የሲቪል ማህበረሰብ እና የሃይማኖት ድርጅቶች

ማንኛዉም የሃይማኖት ድርጅት ወይም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የስራዉ አካል አድርጎ ገንዘብ የሚሰበስብ፣ የሚቀበል፣ የሚሰጥ ወይም የሚያስተላልፍ ከሆነ ገንዘቡ ሽብርተኝነትን በገንዘብ ለመርዳት አለመዋሉን ወይም በወንጀል የተገኘ

ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወንጀል ጋር ያልተያያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ አገልግሎቱ በራሱ ወይም ከሚመለከተዉ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ጋር በመተባበር አግባብነት ያለዉ አጠቃላይ ቁጥጥር በአገልግሎቱ ይደረግበታል።

## ክፍል አራት

## በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ስለመከታተል

### 20.የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር

አገልግሎቱ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተሠጡት ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆኖ፡-

1) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ስጋቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በዚህ አዋጅ መሰረት ይሰበስባል፣ ይቀበላል፣ ያከማቻል፣ ያጠናል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤ እንዲሁም የኢኮኖሚ ደህንነት ስራ ይሰራል፡፡

2) የፋይናንስ፣ የኢኮኖሚ እንዲሁም ንብረት ነክ የሆኑ ጉዳዮችን ሕግ ከማስከበር አንፃር ይከታተላል፡፡

3) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር በተያያዘ የህዝቡ ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፤

4) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን መነሻ፣ የአፈጻጸም ስልት፣ ዓይነት፣ ባህሪ እና ስጋት ያጠናል፤ ለሚመለከታቸዉ አካላትም የመፍትሔ አቅጣጫ ይጠቁማል፤

5) የፋይናንስ ተቋማትን በመቆጣጠር ረገድ ለብሔራዊ ባንክ የተሰጠዉ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፋይናንስ ተቋማት ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰልን እና ሽብርተኝነትን

በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ በዚህ አዋጅ የተመለከቱ ግዴታዎቻቸዉን ለመወጣት የሚረዷቸዉ የአሰራር መመሪያዎችን ያወጣል፤

6) ለብሔራዊ ባንክ የተሰጠዉ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፋይናንስ ተቋማት በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዙ ጉድለቶችን ለማስተካከል በዚህ አዋጅ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) (ለ) እና (መ) የተቀመጡ አስተዳደራዊ ቅጣቶችን ይጥላል፡፡

7) በዚህ አዋጅ መሰረት ያገኛቸዉን በቀላሉ ለጉዳት የሚጋለጡና ሚስጥራዊ መረጃዎችን ለመቀበል የሚያስችል ተገቢ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ይዘረጋል፤

8) በአዋጁ መሰረት የተቀበላቸዉን ሪፖርቶች፣ ለሕግ አስፈፃሚ አካላት የተመሩ ጉዳዮችን፣ ከተመሩት ዉስጥ ምርመራ የተካሔደባቸዉንና ክስ የተመሰረተባቸዉ፤ የወንጀል ጉዳዮችን፤ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠባቸውን እና ዓለም አቀፍ ድጋፍ የተጠየቀባቸዉና መልስ የተሰጠባቸው ጉዳዮችን ጨምሮ ስራዉን በተመለከተ የተሟላ ስታትስቲክስ ይይዛል፤

9) የደረሰዉ ሪፖርት ወይም መረጃ በአገልግሎቱ ግምገማ በዚህ አዋጅ ከተመለከቱት ወንጀሎች ዉጭ ከሆነ ሌላ ወንጀል ጋር በተያያዘ ምርመራ ለማካሄድ ወይም ክስ ለመመስረት የሚያስችል መሆኑን በበቂ ምክንያት ከጠረጠረ ጉዳዩን ወዲያዉኑ አግባብ ላለዉ ሕግ አስፈፃሚ አካል ይመራል፤

10) የዚህን አዋጅ ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ በራሱ ወይም ከሚመለከታቸዉ ተቆጣጣሪ ባለስልጣናት ጋር በመተባበር የፋይናንስ ተቋማት ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎችና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ላይ ቁጥጥር፣ ፍተሻና ክትትል ያደርጋል፤ በተጨማሪም አገልግሎቱ ግዴታዎቻቸዉን እየተወጡ እንዳልሆኑ ወይም ያልተወጡ መሆናቸዉን ሲደረስበት ይህንኑ ለሚመለከታቸዉ ተቆጣጣሪ አካላት ያሳዉቃል።

11)በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ከመከላከል ጋር በተያያዘ ሌሎች ተቋማት የሚያከናዉኗቸዉን ሥራዎች ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

12)ከስራዉ ጋር ግንኙነት ያላቸዉንና በሌሎች ህጎች የተሰጡ ስራዎች ያከናዉናል።

## 21.ከዉጭ አገር መሰል ተቋማት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት

1) አገልግሎቱ ተመሳሳይ ተልዕኮ ካለዉና ተመሳሳይ የሚስጥር አጠባበቅ ደረጃ ከሚከተል የሌላ አገር መሰል ተቋም ጋር በእንካ ለእንካ መርህ ላይ ተመስርቶ የመረጃ ልዉዉጥ ሊያደርግ ወይም በሌላ መንገድ ሊተባበር ይችላል።

2) አገልግሎቱ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም አላማ ከሌላዉ አገር መሰል ተቋም ጋር ስምምነት ሊፈራረም ይችላል።

3) በዚህ አንቀጽ መሰረት የተገኘ መረጃ በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል አመንጪ ወንጀሎችን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዓላማ ብቻ ይዉላል።

## 22.መረጃ ስለማግኘት

1) አገልግሎቱ ስራዉን ለማከናወን የሚያስፈልገዉን ተጨማሪ መረጃ በዚህ አዋጅ መሰረት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ካለበት ማንኛዉም ሰዉ የማግኘት ስልጣን ይኖረዋል።

2) የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚደረገዉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 2(9) (መ) እና አንቀጽ 23 (2) የተደነገጉት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነዉ ነው።

3) አገልግሎቱ ከደረሰዉ ሪፖርት ጋር ተያያዞ ለሥራዉ ያስፈልገኛል ብሎ የሚገምተዉን ተጨማሪ መረጃ ከሚከተሉት አካላት ጠይቆ ማግኘት ይችላል፤

ሀ. ከፖሊስ ክፍሎች

ለ. ይህ አዋጅ የሚፈጸምባቸዉ ሰዎች የመቆጣጠር ሃላፊነት ካለባቸዉ አካላት፤

ሐ. ከሌሎች የመንግስት አካላትና የግል ተቋማት

4) አገልግሎቱ የሌላ አገር መሰል ተቋምን ጥያቄ መሰረት አድርጎ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተመለከቱትን መረጃዎች ማግኘት ይችላል።

5) አገልግሎቱ ስራዉን ለማከናወን የሚያስፈልገዉን መረጃ በዚህ አዋጅ መሰረት ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ ካለበት የፋይናንስ ተቋም በጠየቀ ጊዜ ለሕግ ማስከበር ኦፊሰር በማቅረብ እንዲፈጸም ማድረግ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አለባቸው፡፡

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌን ተፈጻሚ ለማድረግ የፋይናንስ ተቋማት ለሕግ ማስከበር ኦፊሰሩ በፋይናንስ ተቋሙ የሚከናወን ግብይት ማግኘት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አለባቸው፡፡

## 23.የጥርጣሬ ግብይት ሪፖርት ስለማድረግ

1) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ገንዘብ ወይም ንብረት የወንጀል ፍሬ ስለመሆኑ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ወይም የተገናኘ ወይም ለዚሁ ተግባር ሊዉል የሚችል ስለመሆኑ ሲጠረጥሩ ወይም ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖራቸዉ ወዲያዉኑ ጥርጣሬያቸዉን ለአገልግሎቱ ሪፖርት ማድረግ አለባቸዉ። ይህ ግዴታ ግብይት ለማድረግ የተፈፀመ ሙከራንም ይመለከታል።

2) ጠበቆች፣ ራሳቸዉን ችለዉ የሚሰሩ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎች ደንበኞቻቸዉ ከሕግ አንጻር ሊይዙት የሚገባዉን አቋም በመወሰን ሂደት ወይም ከፍርድ ቤት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ደንበኞቻቸዉን ደግፈዉ ከመከራከር ወይም ከመወከል እንዲሁም ወደ ክርክር እንዲገባ ወይም እንዳይገባ ምክር ከመስጠት ሃላፊነታቸዉ ጋር ተያይዞ የሚያገኟቸዉን መረጃዎች ሪፖረት የማድረግ ግዴታ አይኖርባቸዉም።

3) አገልግሎቱ ሪፖርቶች የሚቀርቡበትን ሥርዓትና ፎርም በመመሪያ ይወስናል።

## 24.የጥሬ ገንዘብ ግብይት ሪፖርት ስለማድረግ

የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በአንድ ጊዜ ወይም የተያያዙ ሆነዉ በተለያየ ጊዜ ቢፈፀሙም ተዳምረዉ በአገልግሎቱ ከተወሰነዉ መጠን በላይ የሆኑ የጥሬ ገንዘብ ግብይቶችን ለአገልግሎቱ ሪፖርት ማድረግ አለባቸዉ።

## 25.ግብይትን ስለማዘግየት

1) የፋይናንስ ተቋማት ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ነዉ ብለዉ የሚጠረጥሩትን ግብይት ጥርጣሬያቸዉን ለአገልግሎቱ ሪፖርት እስከሚያደርጉ ድረስ ከመፈጸም መቆጠብ አለባቸዉ።

2) ግብይትን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከመፈጸም መቆጠብ የማይቻል ሲሆን ወይም ጥርጣሬዉን ለማጣራት በሚደረግ ምርመራ ላይ እንቅፋት የሚፈጥር ሲሆን የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ግብይቱን ፈጽመዉ ጥርጣሪያቸዉን ወዲያዉኑ ለአገልግሎቱ ሪፖርት ማድረግ አለባቸዉ።

3) አገልግሎቱ ከጉዳዩ ክብደት የተነሳ አስፈለጊ ሆኖ ሲያገኘዉ አጠራጣሪ የሆነን ግብይት ከሰባት የስራ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ እንዲታገድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌን መሰረት የደረሰውን የእግድ ትዕዛዝ ያለምንም መዘግየት የሕግ ማስከበር ኦፊሰሩ መፈጸም አለበት፡፡

## 26.መረጃን አሳልፎ መስጠትን ስለመከልከል

1) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች ፣ ዳይሬክተሮቻቸዉ፣ ሃላፊዎቻቸዉ እና ሰራተኞቻቸዉ፡-

ሀ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ጥርጣሬን የሚመለከት መረጃ ለአገልግሎቱ ሊሰጥ መሆኑን ወይም በመስጠት ላይ ወይም የተሰጠ መሆኑን፤ ወይም

ለ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ምርመራ ሊካሄድ መሆኑን ወይም በመካሄድ ላይ ወይም የተካሄደ መሆኑን፤

የሚመለከት መረጃ ለደንበኞች ወይም ለሦስተኛ ወገኖች በምንም ሁኔታ መስጠት የለባቸዉም።

2) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች በፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ሥራዎች፣ ዳይሬክተሮች፣ ሃላፊዎች፣ ሰራተኞችና የሕግ አማካሪዎች እና አግባብ ባላቸዉ ባለስልጣናት መካከል በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ጥርጣሬን የሚመለከት መረጃ መግለፅን ወይም መለዋወጥን የሚከለክሉ አይሆንም።

## 27.በጥርጣሬ ሪፖርት ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ

አገልግሎቱ በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመጠርጠር በቂ ምክንያት ሲኖረዉ የሚመለከተዉ ወንጀል መርማሪ አካል በቀጣይ ስለሚወሰደዉ እርምጃ እንዲወስን አግባብ ያለዉን መረጃ ያስተላልፍለታል።

## 28.የተቆጣጣሪ ባለስልጣኖች ስልጣን እና ተግባር

1) ተቆጣጣሪ ባለስልጣን የፋይናንስ ተቋማት እና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድ የሙያ ስራዎች በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ግዴታዎች አክብረዉ መስራታቸዉን መቆጣጠር አለባቸዉ፡፡

2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቆጣጣሪ ባለስልጣኖች፡-

ሀ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል፣ አመንጭ ወንጀሎችን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በመመርመርና በመክሰስ ረገድ ከሌሎች አግባብ ካላቸዉ ባለስልጣኖች ጋር ይተባበራሉ፣ መረጃ ይለዋወጣሉ፤

ለ. በዉጭ አገር የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት ቅርንጫፎች እና የአብዛኛዉ አክስዮን ባለድርሻ የሆኑባቸዉ ተቋማት የአገሩ ህጎች እስከፈቀዱ ድረስ ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣሙ እርምጃዎችን መቀየሳቸዉንና መተግበራቸዉን ያረጋግጣሉ፤

ሐ. በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር ሊገናኙ የሚችሉ ግብይቶችን ወይም ድርጊቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በፍጥነት ለአገልግሎቱ ሪፖርት ያደርጋሉ፡

መ. የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች በማስፈጸም ረገድ የተወሰዱ እርምጃዎችና የተጣሉ ቅጣቶችን በሚመለከት የስታትስቲክስ መረጃዎችን ይይዛሉ፡፡

3) ተቆጣጣሪ ባለስልጣኖች የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በፋይናንስ ተቋማትና የፋይናንስ ነክ ባልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች መጣሳቸዉን ሲያረጋግጡ ከሚከተሉት መካከል አንዱን ወይም ከዚህ በላይ የሆኑትን እርምጃዎችና ቅጣቶች መወሰን ይችላሉ፡-

ሀ. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ. የተወሰነ መመሪያ እንዲከበር ማዘዝ፤

ሐ. የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች እየወሰዱ‌ቸዉ ስላሉ እርምጃዎች በየጊዜዉ ሪፖረት እንዲያደርጉ ማዘዝ፤

መ. የፋይናንስ ተቋማትን ከሁለት መቶ ሺህ ባላነሰና ከአምስት ሚሊዮን ባልበለጠ፣ ለሪልስቴት አልሚዎችና ወኪሎች ከሁለት መቶ ሺ ባላነሰና ከሁለት ሚሊዬን ባልበለጠ እና ለሌሎች ፋይናንስ ነክ ላልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች ከብር አስር ሺ ባላነሰ እና ከብር አንድ መቶ ሺህ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ መቅጣት፤

ሠ. ግለሰቦችን በንግዱ ወይም በሙያ ዘርፍ ተቀጥረዉ እንዳይሰሩ መከልከል፤

ረ. ጊዜያዊ አስተዳዳሪ መመደብን ጨምሮ የስራ አስኪያጆችን፣ የዳይሬክተሮችን እና በወሳኝነት የመቆጣጠር ስልጣን የሚኖራቸዉን ባለቤቶች ስልጣን መገደብ፤

ሰ. ፈቃድ ማገድ ወይም መሰረዝና በስራዉ ወይም በሙያዉ መስራት መቀጠልን መከልከል ፤ ወይም

ሸ. አግባብነት ያላቸዉ ሌሎች እርምጃዎች መዉሰድ ፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የተቋም ስራ አስኪያጅ በከፊል ወይም በሙሉ ስራዉን እንዳያከናዉን የተደረገ ክልከላ ወይም በሙሉ ስራዉን ወይም ክልከላዉን ለማንሳት የተወሰደ እርምጃ በንግድ መዝገብ እንዲመዘገብ የሚመለከተዉ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን አግባብ ላለዉ አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) (ለ) እና (መ) መሰረት በፋናይንስ ተቋማት ላይ የሚጣል አስተዳደራዊ ቅጣት በፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት የሚተገበር ይሆናል፡፡

6) የተቆጣጣሪ ባለስልጣኖች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የሚወስዷቸዉን እርምጃዎችና ቅጣቶች ለአገልግሎቱ ማሳወቅ አለባቸዉ፡፡

**29.ሚስጥር ስለመጠበቅ**

በአገልግሎቱ ዘንድ የሚገኝ መረጃ በተገቢዉና በህጋዊ መንገድ በእጃቸዉ የገባ የአገልግሎቱ ሃላፊዎች፣ ሰራተኞች በትዉስት ከሌላ ቦታ ተመድበዉ በአገልግሎቱ የሚሰሩ ሰራተኞች ወይም ሌሎች ሰዎች በዚህ አዋጅ በተደነገገዉ መሰረት ካልሆነ በቀር መረጃዉን ለሌሎች ሰዎች መግለጽ አይችሉም፡፡

**30.ሚስጠር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታን ወይም ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም ስለመከልከሉ**

በዚህ አዋጅ መሰረት መረጃ የመስጠት ወይም ተያያዥነት ያለዉ ሰነድ የማቅረብ ግዴታን ላለመወጣት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25(2) በተደነገገዉ መሰረት ካልሆነ

በስተቀር ሚስጥር የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታን ወይም ልዩ መብትን በምክንያትነት መጠቀም አይችልም፡፡

## 31.ከተጠያቂነት ነጻ ስለመሆን

1) በዚህ አዋጅ መሰረት በቅን ልቦና መረጃ በሚሰጡ ወይም ሪፖርት በሚያደርጉ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች ላይ ወይም በዳይሬክተሮቻቸዉ፣ በሃላፊዎቻቸዉ ወይም በሰራተኞቻቸዉ ላይ የባንክ ስራ ወይም የሙያ ሚስጥር ወይም የዉል ግዴታ ተጥሷል በሚል የወንጀል ፣ የፍትሐ ብሄር ወይም አስተዳደራዊ ክስ ሊቀርብባቸዉ አይችልም፡፡

2) በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ 23 እስከ 25 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት በቅን ልቦና ሪፖርት እስከተደረገ ድረስ ጥርጣሬ ያስከተለን ግብይት በፈጸሙ የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች ላይ ወይም በዳይሬክተሮቻቸዉ ፣ በሃላፊዎቻቸዉ ወይም በሰራተኞቻቸዉ ላይ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀል ክስ ሊቀርብባቸዉ አይችልም፡፡

3) የአገልግሎቱ ወይም የተቆጣጣሪ ባለስልጣን ሃላፊዎች፣ ሰራተኞችና በትዉስት ከሌላ ቦታ ተመድበዉ የሚሰሩ ሰራተኞች ይህን አዋጅ ወይም በአዋጅ መሰረት የወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች ለማስፈጸም ሲባል በቅን ልቦና ለሚፈጽሙት ማንኛዉም ድርጊት በፍትሐ ብሄር፣ በወንጀል ወይም በአስተዳደራዊ ሃላፊነት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## ክፍል አምስት

## ስለምርመራ

## 32. የምርመራ ዘዴ

1) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን ወይም የወንጀል ፍሬን ተከታትሎ ለመለየት የዳኝነት አካላት ለተወሰነ ጊዜ፡-

ሀ. በባንክ ሂሳቦች እና በሌሎች ተመሳሳይ ሂሳቦች ላይ ክትትል ለማድረግ፤

ለ. የኮምፒዉተር ሥርዓቶችን፣ መረቦችንና ሰርቨሮችን ለመለየት፣

ሐ. መገናኛዎችን በክትትል ሥር ለማዋል ወይም ለመጥለፍ፤

መ. ድርጊቶችን፣ ባህሪዎችንና ንግግሮችን በድምፅ እና በምስል ለመቅረፅና ፎቶ ግራፍ ለማንሳት፤

ሠ. የደብዳቤ ልዉዉጦችን ለመጥለፍ እና ለመያዝ፤

ረ. በሽፋን ሥር ስለሚደረግ ምርመራና በቁጥጥር ስር የሚደረግ ማስተላለፍ ለመጠቀም፤

የሚያስችል ትዕዛዝ ለወንጀል መርማሪ አካላት መስጠት ይችላሉ፡፡

2) የመርማሪ አካል በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተደነገጉ የማስረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ የሚችለዉ ፍርድ ቤት አስተማማኝ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ ሲፈቅድ ብቻ ነዉ።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም መርማሪ አካል አስቸኳይ ሁኔታ ካጋጠመው በአካባቢው ያለውንና የሚመለከተውን የዓቃቤ ሕግ ተቋም የበላይ ኃላፊ በማስፈቀድ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የምርመራ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስረጃ ሊሰበስብ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት መርማሪ አካል ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ የምርመራ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስረጃ ለመሰብሰብ በጀመረ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ ምክንያቶቹንና በዓቃቤ ሕግ የተሰጠውን ጊዜያዊ ፈቃድ ጨምሮ ለፍርድ ቤት በፅሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል። ፍርድ ቤቱም የጥያቄውን አግባብነት መርምሮ ለመቀበል ወይም ውድቅ ለማድረግ ይችላል፡፡

5) ፍርድ ቤት የምርመራ ዘዴ ማስረጃ እንዲሰበስብ ለመርማሪ አካል ፈቃድ ሲሰጥ፡-

6) ሀ. ማስረጃ ስለሚሰበሰብበት ዘዴ እና ስለሚከናወንበት አግባብ፤

7) ለ. የሚከናወንበት ጊዜ በተመለከተ ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

8) የማስረጃ ማሰባሰቢያው ዘዴ ጠለፋ ወይም ክትትል እንደሆነ ጠለፋዉ ወይም ክትትሉ የሚደረግበትን የስልክ፤ የፋክስ፤ የሬዲዮ፤ የኢንተርኔት፤ የኤሌክትሮኒክስ፤

የፓስታና የመሳሰሉትን የግንኙነት መስመሮች አድራሻ ወይም መለያ መጥቀስ አለበት፡፡

9) ማንኛውም የመገናኛ አገልግሎት አቅራቢ በመርማሪ አካል ጠለፋውን ለማካሄድ ሲጠየቅ ጠለፋው በፍርድ ቤት ወይም በአቃቤ ሕግ የበላይ ሃላፊ የተፈቀደ መሆኑን በማረጋገጥ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለበት፡፡

10)በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር በሕግ አስከባሪ አካላት በጠለፋ የተገኘ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ በጠለፋ በተገኘበት መልክ በቀጥታ ካልቀረበ በቀር ዋጋ አይኖረውም፡፡

11)ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ መሰረት የምርመራ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስረጃ ለማሰባሰብ የሚፈቅደው ጊዜ ከ ፺ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡ መርማሪ አካል በተሰጠው ጊዜ ውስጥ የሚፈለገውን ማስረጃ ያላገኘ እና የምርመራው ዘዴዎቹን መጠቀሙ ተጨማሪ ጊዜ አስፈላጊ ለመሆኑ በቂ ምክንያት ያለው ከሆነ ፍርድ ቤቱን ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም መርማሪዉ ያከናወነውን ተግባር፣ የተፈቀደው ዘዴ እያስገኘ ያለውን ውጤት በማገናዘብ እና አስፈላጊ መሆኑን በመመርመር ፍርድ ቤቱ ለሰላሳ ቀን ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡

12)በዚህ አንቀጽ መሰረት የምርመራ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚቀርብ ጥያቄ፣ በፍርድ ቤት የሚሰጠው ፈቃድ፣ የምርመራ ዘዴዎች እና በምርመራ ዘዴው የተገኙ መረጃዎችና ማስረጃዎች የማሰባሰቡ ሁኔታ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በፖሊስ፣ ዓቃቤ ሕግ ፣ በፍርድ ቤት እና መረጃው የደረሳቸው ሌሎች አካላት በሚስጥር መያዝ አለበት፡፡ ማስረጃ ማሰባሰቡ ከተጠናቀቀ በኋላም ለጉዳዩ በማስረጃነት የሚያገለግሉ ካልሆነ በስተቀር በምርመራ ዘዴው የተገኙት መረጃዎች መወገድ አለባቸው፡፡

13) የወንጀል ድርጊት የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና የአመንጭ ወንጀሉ ምርመራ በትይዩ ይከናወናል፡፡

14)የንብረቱ ባለቤት የንብረት ምርመራ እየተካሄደበት መሆኑን እንዳያውቅ መርማሪው ተገቢውን የቅድመ ጥንቃቄ እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

**33.በሽፋን ሥር ስለሚደረግ ምርመራና በቁጥጥር ስር የሚደረግ ማስተላለፍ**

1) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልን የመመርመር ሃላፊነት የተሰጠዉ ሰዉ እነዚህን ወንጀሎች የሚመለከት ማስረጃ ለማግኘት ወይም የወንጀል ፍሬን ተከታትሎ ለመለየት ሲባል በሽፋን ስር ከሚደረግ ምርመራና በቁጥጥር ስር ከሚደረግ ማስተላለፍ ጋር ተያይዞ የሚፈጽመዉ ድርጊት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ወንጀል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀልነት ሊፈረጅ የሚችል ቢሆንም የወንጀል ክስ አይቀርብበትም።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተዉን አሰራር ለመከተል በቅድሚያ የፍርድ ቤት ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ መሰረት በሽፋን ስር የሚደረግ ምርመራ ወይም በቁጥጥር ስር የሚደረግ ማስተላለፍን እንዲያስፈጽም የተመደበ ሰዉ ተጠርጣሪዉ ማንኛዉንም ወንጀል እንዲፈጽም መገፋፋት የለበትም፡፡

4) በዚህ አዋጅ መሰረት በሽፋን ስር የሚደረግ ምርመራ ወይም በቁጥጥር ሰር የሚደረግ ማስተላለፍን እንዲያስፈጽም የተመደበ ሰዉ በግዴታው ላይ እያለ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያትና ከፈቃዱ ውጭ ሆኖ ለሚፈጽመው የወንጀል ድርጊት የወንጀል ክስ አይቀርብበትም።

## 34.እንዳይታወቅ የተደረገ ምስክር

1) ፍርድ ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በምስክሩ ወይም በዓቃቤ ሕግ ጥያቄ ላይ ተመስርቶ ምስክሩ ወይም የቤተሰቡ አባል በምስክርነቱ ምክንያት ለአደጋ የሚጋለጥ መሆኑን ሲረዳ የምስክሩ ማንነት በሚስጥር እንዲያዝ ሊወሰን ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የምስክር ማንነት በሚስጥር ተይዞ የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል የሚደረገዉ ሌሎች የምርመራ ዘዴዎችን መጠቀም እዉነቱ ላይ ለመድረስ በቂ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ብቻ ነዉ፡፡

## 35.ሽብርተኝነትን በገንዘብ ከመርዳት ጋር የተያያዘ ገንዘብን ስለማገድ

1) የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት በተባበሩት መንግስታት ቻርተር ምዕራፍ ሰባት መሰረት የሰየማቸው አሸባሪዎች፣ አሸባሪዎችን በገንዘብ የሚረዱ እና ሽብርተኛ ድርጅቶች ገንዘብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ ይታገዳል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በተሰየመው ሰው ባለቤትነት፣ ይዞታ ወይም ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ቁጥጥር ስር ያለ ሃብት ሳይዘገይ በአገልግሎቱ ውሳኔ መታገድ አለበት፡፡

3) አገልግሎቱ የተሰየመ ወይም የፍርድ ውሳኔ የተላለፈበትን ሰው ዝርዝርና የዝርዝሩን ማሻሻያዎች ሃላፊነት ላለባቸው ሰዎች እና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ሳይዘገይ ማሰራጨት አለበት፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለህዝብ ግልጽ ያደርጋል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጠው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ እግዱ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎችና ሁኔታዎች እና ጸንቶ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ የሚገልጽ ሆኖ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ታትሞ መውጣት አለበት፡፡

5) የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች ያለምንም መዘግየትና ቅድመ ሁኔታ፡-

   ሀ. በእጃቸው የሚገኘውንና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም 2 ከተጠቀሱት ግለሰቦችና አካላት ጋር ግንኙነት ያለውን ገንዘብ ወድያውኑ እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ፤ እና

   ለ. የተባለው ገንዘብ በእጃቸው መኖሩን ሳይዘገዩ ለአገልግሎቱ ሪፖርት ማድረግ ፤አለባቸው፡፡

## ክፍል ስድስት

## ዓለም አቀፍ ትብብር

### 36.ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1) የፍትህ ሚኒስቴር ለዚህ አዋጅ አላማ ሲባል የአለም ዓቀፍ ትብብር ማእከላዊ ባለስልጣን ነው።

2) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት ወንጀሎችን በሚመለከት ወንጀለኛን አሳልፎ በመስጠት፣ በመመርመርና ለፍርድ በማቅረብ ረገድ ከሌሎች አገሮች አግባብ ያላቸው ባለስልጣኖች ጋር ቅድሚያ በመስጠት መርህ እና በተፋጠነ ሂደት ሁሉ የጋራ የሕግ ድጋፍ ትብብር ማድረግ አለባቸው፡፡

3) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አላማ እንደ ፖለቲካ ወንጀል፣ ከፖለቲካ ወንጀል ጋር ግንኙነት እንዳለው ወንጀል ወይም በፖለቲካ ፍላጎት በመገፋፋት እንደተፈጸመ ወንጀል አይቆጠርም፡፡

4) አግባብ ያላቸው ባለስልጣኖች በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶችን በሚመለከት መሰረታዊ፣ ተጠቃሚ ስለሆኑ ባለቤቶቻቸው መረጃዎች ወይም ተጠቃሚ የሚሆኑ ባለቤቶቻቸው ከሀገር ውጪ የሚገኙበትን አድራሻ በሚመለከት የጋራ የሕግ ድጋፍ ትብብር ሲልኩም ሆነ ሲቀበሉ የተቀበሉትን ምላሽ ጥራት መቆጣጠር አለባቸው፡፡

## 37. የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ

1) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በሚመለከት የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ በሌላ አገር አመልካችነት ሲቀርብ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሰረት ይስተናገዳል፡፡

2) የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ በተለይ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

ሀ. ከሰዎች ማስረጃ ወይም ቃል መቀበልን፤

ለ. የተያዙ ሰዎችን ወይም ፍቃደኛ የሆኑ ምስክሮችን ማስረጃ እዲሰጡ ወይም ምርመራውን እንዲረዱ ለጠያቂው ሀገር የዳኝነት አካላት ማቅረብን፤

ሐ. የፍርድ ቤት ሰነዶችን ለሚመለከታቸው እንዲደርሱ ማድረግን፤

መ. የፍተሻና የመያዝ ትዕዛዞችን ማስፈጸምን፤

ሠ. ቁሳቁሶችንና ሥፍራዎችን መፈተሸን፤

ረ. መረጃዎችን፤ የማስረጃ ቁሳቁሶችንና የባለሙያ ግምቶችን መስጠትን፤

ሰ. የመንግስት፤ የባንክ፣ የፋይናንስ፣ የተቋም ወይም የንግድ ስራ መዝገቦችን ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላትን ተጠቃሚ ስለሚሆኑ እና ስለ አመራር መዋቅራቸው በተመለከተ መሰረታዊ መረጃን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶችና መዝገቦች ዋና ወይም የተረጋገጡ ቅጅዎችን መስጠትን፤

ሸ. የወንጀል ፍሬን፣ የወንጀል መፈጸሚያዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ለማስረጃነት አላማ ተከታትሎ መለየትን ወይም ማግኘትን፤

ተ. ሌሎች ከኢትዮጵያ ሕጎች ጋር የማይቃረኑ የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄዎች፡፡

## 38. ድጋፍ ስለመከልከል

1) የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄ ተቀባይነት ሊነፈገው የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ይሆናል፡-

   ሀ. በጠያቂው አገር ሕግ መሰረት አግባብ ባለው አካል የቀረበ ጥያቄ ካልሆነ ወይም ይዘቱ በመሰረታዊ ደረጃ ከዚህ አዋጅ አንቀጽ 45 ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም ካልሆነ፤

   ለ. አፈጻጸሙ የኢትዮጵያን ሕግና ሥርዓት፣ ሉዓላዊነት፣ ደህንነት፣ የህዝብ ጥቅም ወይም ሌሎች መሰረታዊ ጥቅሞችን የሚነካ ከሆነ፤

   ሐ. ጥያቄው የሚመለከተው የወንጀል ድርጊት በኢትዮጵያ ውስጥ በመዳኘት ላይ ከሆነ ወይም የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፣

   መ. እርምጃው ወይም ትዕዛዙ በተፈላጊው ግለሰብ ላይ ያነጣጠረው በግለሰቡ ዘር፣ ሃይማኖት፣ ዜግነት፣ የዘር ሀረግ፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ጾታ ወይም አቋም ላይ ብቻ ተመስርቶ መሆኑን ለማመን የሚያስችል ተጨባጭ ምክንያት ሲኖር፤

ሠ. በድጋፍ ጥያቄው ውስጥ የተጠቀሰው ወንጀል በኢትዮጵያ ሕግ በወንጀልነት የተፈረጀ ካልሆነ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ወንጀል ጋር የሚያመሳስለው ባህሪ የሌለው ከሆነ፤

ረ. በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተጠቀሰውን ወንጀል በሚመለከት የተጠየቀውን እርምጃ ወይም ተመሳሳይ ውጤት የሚኖረውን ሌላ እርምጃ መውሰድ የማይፈቀድ ከሆነ፤

ሰ. በኢትዮጵያ ወይም በጠያቂው ሀገር ሕግ በተደነገገ የይርጋ ጊዜ ምክንያት የተጠየቀውን እርምጃ ማዘዝ ወይም መፈጸም የማይፈቀድ ከሆነ፤

ሸ. እንዲፈጸም የተጠየቀውን ውሳኔ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ተፈጻሚ ማድረግ የማይቻል ሲሆን፤ ወይም

ቀ. በውጭ ሀገር የተሰጠው ውሳኔ የተከሳሹን የመከላከል መብት በበቂ ደረጃ ባላስተናገደ ሁኔታ የተሰጠ ከሆነ፡፡

2) መረጃውን የጠየቀው አካል የተላከለትን መረጃ ሚስጥራዊነት ለመጠበቅ ፍቃደኛ ካልሆነ ሊከለከል ይችላል፡፡

3) አግባብ ባለው ባለስልጣን የጋራ ትብብር የሕግ ድጋፍ ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ የቀረበበትን ምክንያት አግባብ ላለው የጠያቂው አገር ባለስልጣን ወድያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 39. የምርመራ ሥራን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ

1) አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ጋር የማይቃረን ለየት ያለ ሥርዓትን ተከትሎ እንዲፈጸም ካልጠየቀ በስተቀር ምርመራ የሚካሄደው በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገገውን የምርመራ ሥርዓት ተከትሎ ነው፡፡

2) የጠያቂው አገር አግባብ ያለው ባለስልጣን የመደበው የመንግስት ሃላፊ የምርመራ ስራውን አፈጻጸም እንዲታዘብ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## 40. ጊዜያዊ እርምጃዎች መውሰድን የሚመለከት የድጋፍ ጥያቄ

1) በጠያቂው አገር እንዲወሰዱ የተጠየቁ ጊዜያዉ እርምጃዎች አግባብ ባለው የኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ይፈጸማሉ፡፡ እንዲወሰዱ የተጠየቁት እርምጃዎች በጥቅል አነጋገር የተገለፁ ከሆነ በሕጉ ከተደነገጉትና ይበልጥ አግባብነት ያለቸው እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

2) የተጠየቁት እርምጃዎች በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉ ካልሆኑ አግባብ ያለው ባለስልጣን በኢትዮጵያ ሕግ የተደነገጉትና በውጤት ይበልጥ ቅርበት ያላቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል።

3) ጊዜያዊ እርምጃዎችን ስለማንሳት በዚህ አንቀጽ 36/3 የተመለከተው ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፤ ሆኖም እርምጃወቹ እንዲነሱ ከመደረጋቸው በፊት አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለስልጣን እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

## 41.አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ

1) በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን በሚመለከት ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን በሆነችበት አግባብ ያለው ዓለም ዓቀፍ ስምምነት በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች መሰረት ይሰተናገዳል፡፡
2) በዚህ አዋጅ መሰረት ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ መስጠት የሚቻለው ለጥያቄው መነሻ የሆነው ወንጀል ወይም ተመሳሳዩ በጠያቂው አገርና በኢትዮጵያ ሕግ በወንጀልነት የተፈረጀ ሲሆን ነው፡፡
3) የጠያቂው አገር ሕግ ወንጀሉን ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ወይም ባልሆነ የወንጀል ምድብ ወይም ስያሜ ቢገልጸውም ድርጊቱ በሁለቱም አገር ህጎች በወንጀልነት የተፈረጀ እስከሆነ ድረስ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡

## 42.አሳልፎ የመስጠት ጥያቄን ስለአለመቀበል

1) የወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የሚከተሉትን ምክንያቶችን ሲኖር ተቀባይነት አይሰጠውም፡-

ሀ. ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰው የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሲሆን፤

ለ. ጥያቄው የቀረበው ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀውን ሰው በፆታው፣ በዘሩ፣ በሃይማኖቱ፣ በዜግነቱ፣ በዘር ሃረጉ ወይም በፖለቲካ አመለካከቱ ሳቢያ ለመክሰስና ለመቅጣት ተፈልጎ መሆኑን ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖር፣

ሐ. አሳልፎ የመስጠት ጥያቄው የቀረበበትን ወንጀል በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን፣

መ. ከሁለቱ አገሮች በአንዳቸው ሕግ መሰረት ምህረትና የይርጋ ጊዜ ገደብን ጨምሮ ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀውን ሰው ከመከሰስ ወይም ከመቅጣት ነፃ የሚያደርግ ማንኛውም ምክንያት ሲኖር፣ ወይም

ሠ. ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰው የማሰቃየት ወይም የጭካኔ ድርጊት ወይም ኢሰብዓዊ ወይም የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የተፈፀመበት ወይም ሊፈፀምበት የሚችል ስለመሆኑ ወይም በሲቪልና የፖሊቲካ መብቶች ዓለም ዓቀፍ ኮንቬንሽን አንቀጽ 14 እንደተደነገገው በወንጀል ፍርድ ሂደት መሠረታዊ መብቶቹን ተነፍጎ እንደነበር ወይም ሊነፈግ እንደሚችል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖር፡፡

2) ወንጀለኛን ወይም ተጠርጣሪን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የሚከተሉት ምክንያቶች ሲኖሩ ተቀባይነት ሊያጣ ይችላል፡-

ሀ. አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የቀረበበትን ወንጀል የሚመለከት ክስ በኢትዮጵያ ውስጥ በመታየት ላይ ሲሆን፣

ለ. አሳልፎ የመስጠት ጥያቄ የቀረበበት ወንጀል የተፈፀመው ከሁለቱም አገሮች የግዛት ክልል ውጪ ሲሆን፣

ሐ. ተላልፎ እንዲሰጥ የተጠየቀው ሰው በፈፀመውና ለጥያቄው መነሻ በሆነው ድርጊት ምክንያት በጠያቂው አገር ውስጥ ባለ መደበኛ ባልሆነ ወይም ፍትሃዊነት በሌለው ልዩ ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት አካል ተፈርዶበት የነበረ ወይም ተከሶ ሊፈረድበት የሚችል ሲሆን፣

መ. የወንጀሉ ሁኔታና የጠያቂው አገር ጥቅሞች ጭምር ተገናዝበው ቢታዩም ተላልፎ እንዲሰጥ ከተጠያቀው ሰው የእድሜ፣ የጤና ወይም ሌሎች የግል

ሁኔታዎች አንፃር ሲታይ አሳልፎ መስጠቱ ከሰብዓዊነት መመዘኛዎች ጋር የማይጣጣም ሆኖ ሲገኝ፤ወይም

ሠ. ጥያቄው ተከሳሹ ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት ስለክሱ በቂ መረጃ ሳይኖረው ወይም ራሱን ለመከላከል በቂ የመዘጋጃ ዕድል ሳይኖረው በሌለበት በተሰጠ የመጨረሻ ፍርድ ላይ ተመስርቶ የቀረበ ከሆነና ክሱ እንደገና ባለበት እንዲታይ ዕድል ያላገኘ ወይም ሊያገኝ የማይችል ሲሆን፤

3) አሳልፎ የመስጠት ጥያቄው ውድቅ የተደረገው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ተራ ፊደል (ሀ) ወይም (ሠ) መሠረት ከሆነ ግለሰቡ ለጥያቄው መነሻ በሆነው ወንጀል እንዲከሰስ ለማድረግ ጉዳዩ አግባብ ላለው ባልስልጣን እንዲተላለፍ ይደረጋል፡፡

43. አሳልፎ የመስጠት ቀላል ሥርዓት

ተላልፎ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበት ሰው አግባብ ያለው ባለስልጣን ፊት ቀርቦ ተላልፎ እንዲሰጥ በመደረጉ መስማማቱን በግልጽ ካሳወቀ አሳልፎ መሰጠቱ ተጨማሪ ሥነ ሥርዓት መከተል ሳያስፈልግ ይፈቀዳል፡፡

44.የጥያቄዎች ይዘት

1) የሚቀርቡ ጥያቄዎች ይዘት የሚከተሉትን መግለጽ አለበት፡-

ሀ. ጥያቄውን ያቀረበው ባለሥልጣን ማንነት፤

ለ. የምርመራውን፤ የክሱን ወይም የፍርድ ሂደቱን የሚያካሂደውን ባለሥልጣን ስም፤

ሐ. ጥያቄው የቀረበለትን ባለሥልጣን፤

መ. የጥያቄውን ዓላማና ማንኛውንም አግባብነት ያለው ተያያዥ መግለጫ፤

ሠ. ለጥያቄው ደጋፊ የሆኑ መረጃዎችን፤

ረ. የሚመለከተውን ሰው ማንነት ለመለየት የሚረዳ ማንኛውንም የሚታወቅ ዝርዝር መግለጫ በተለይም የግለሰቡን ስም፤ የጋብቻ ሁኔታ፤ ዜግነት፤ አድራሻና የሚገኝበትን ሥፍራ እና መረጃ፤

ሰ. የሚመለከተውን ሰው የወንጀል መፈፀሚያ፣ ገንዘብ ወይም ንብረት ለመለየትና ለመከታተል የሚያስፈልግ ማንኛውንም መረጃ፣

ሸ. ወንጀሉን የሚያቋቁመውን የሕግ ድንጋጌ ይዘት፣ ወይም አግባብነት ያለው ከሆነ በወንጀሉ ላይ ተፈፃሚነት የሚኖረውን ሕግና ወንጀሉ ሊያስከትል የሚችለውን ቅጣት የሚመለከት መግለጫ፣ እና

ቀ. የተጠየቀውን ድጋፍ ዓይነት የሚያመለክት መግለጫ፣

2) የተወሰኑ የድጋፍ ዓይነቶችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች በተጨማሪ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ አለባቸው፣

ሀ. ጊዜያዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ የሚጠይቅ ሲሆን የሚፈለጉትን እርምጃዎች የሚያመለክት መግለጫ፣

ለ. የመውረሻ ትዕዛዝ ለማሰጠት የሚቀርብ ጥያቄ ሲሆን የዳኝነት አካላት በአገሪቱ ሕግ መሠረት ትዕዛዙን ለማሰጠት የሚያስችሏቸውን መረጃዎችንና የመከራከሪያ ነጥቦችን የያዘ መግለጫ፣

ሐ. ጊዜያዊ እርምጃዎችን የሚመለከት ትዕዛዝ ወይም የመውረሻ ትዕዛዝ እንዲፈፀም የሚጠየቅ ሲሆን፡-

1. የትዕዛዙን የተረጋገጠ ቅጂ እና በትዕዛዙ ውስጥ ያልተካተቱ ከሆነ ትዕዛዙን ለመስጠት ያስቻሉትን ምክንያቶች የሚያሳይ መግለጫ፣
2. ትዕዛዙ ተፈፃሚነት ያለውና መደበኛ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ያለመሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ፣ እና
3. አስፈላጊና የሚቻል ሲሆን በገንዘቡ ወይም ንብረቱ ላይ ሊቀርቡ የሚችሉ የሶስተኛ ወገን የመብት ጥያቄዎችን፣

መ. ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ጥያቄው በወንጀሉ የተፈረደበትን ሰው የሚመለከት ሲሆን የፍርድ ውሳኔውን ዋና ወይም የተረጋገጠ ቅጂ ወይም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔውን፣ ቅጣቱ የሚኖረውን ተፈፃሚነት እና ያልተፈጸመውን ቀሪ የቅጣት መጠን የሚያሳይ ማንኛውንም ሰነድ፡፡

3) ጥያቄዎችና አባሪዎቻቸው በፌደራል የስራ ቋንቋ እና በእንግሊዝኛ ትርጉማቸው ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

**45.ተጨማሪ መረጃዎች**

ጉዳዩን በማየት ላይ ያለው አግባብ ያለው ባለስልጣን ትዕዛዙን ለመፈፀም የሚያስፈልግ ወይም የሚረዳ ሆኖ ሲያገኘው አግባብ ያለው የጠያቂው አገር ባለሥልጣን ተጨማሪ መረጃዎች እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**46. ሚስጥር ስለመጠበቅ**

ጥያቄው መቅረቡ ወይም ይዘቱ በሚስጥር እንዲያዝ በጥያቄው ውስጥ የተገለጸ ከሆነ ይኸው መከበር ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩን በሚስጥር መያዙ የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ ወዲያኑ ጠያቂው አገር እንዲያውቀው መደረግ አለበት፡፡

**47. ጥያቄ ማስተናገድን ስለማዘግየት**

እንዲፈፀም የተጠየቀው እርምጃ ወይም ትዕዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄድ ምርምራ ወይም የክስ ሂደት ላይ በመሠረታዊ ደረጃ ጣልቃ የሚያስገባ ሲሆን አግባብነት ያለው ባለሥልጣን ጉዳዩን ሊያዘገየው ይችላል፡፡ ይህንኑም ለጠያቂው አገር አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወድያውኑ ያሳውቃል፡፡

**48. ሌሎች አለም ዓቀፍ ግንኙነቶች**

1) የዚህ አዋጅ  አንቀጽ 36 (1) ድንጋጌ ቢኖርም በአገልግሎቱ በሚወጣው ዝርዝር መመሪያ መሰረት አግባብነት ያላቸው ባለስልጣናት በወንጀል የተገኘ ንብረት ሕጋዊ ማስመሰል፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት እንዲሁም የአመንጪ ወንጀል ጋር በተገናኘ  አግባብነት ካለው የውጭ ሀገር ባለስልጣን አቻ ለአቻ በሆነ ግንኙነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም ሲጠየቁ  የቁጥጥር፣ ፍተሻ ክትትል ስራ ውጤቶችን እና ሌሎች መረጃን መስጠት፣ መቀበል ወይም መጠየቅ ይችላሉ፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት የአቻ ለአቻ ትብብርን በተመለከተ መረጃ ስለሚለዋወጡበት ቅድሚያ ስለሚሰጡበት እና የቀረበ የትብብር

ጥያቄዎችን ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ስለሚፈጽሙበት አግባብ ለመወሰን በአገልግሎቱ መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 49. የማስረጃዎች ተቀባይነት

በዚህ አዋጅ መሰረት የተያዘን መረጃ የሚመለከት ሰነድ ወይም የሰነዱ የተረጋገጠ ግልባጭ ወይም የተረጋገጠ የኤሌክትሮኒክ ህትመት በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ላለ ጉዳይ በማስረጃት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

### 50.ስለ ይርጋ ጊዜ

በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወይም ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀል በፈጸመ ሰው ላይ የሚቀረብ ክስና የሚጣል ቅጣት እንዲሁም ንብረት መውረስ በይርጋ አይታገድም፡፡

### 51.ስልጠና እና ሌሎች እገልግሎቶቸ

1) በዚህ አዋጀ አንቀጽ 18 መሰረት ሕግ የማስከበር ክፍል ሰራተኞች የሚወስዱት ስልጠና እና እውቀና በእገልግሎቱ የሚሰጥ ይሆናል።

2) ሕግ የማስከበር ክፍል የማቋቋም ሃላፊነት ያለባችው የፋይናንስ ተቋማትና ፋይናንስ ነክ ያልሆኑ የተሰየሙ የንግድና የሙያ ስራዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለሚሰጣቸው አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ምክፍል አለባችው። ዝርዝሩ በአገልግሎቱ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

3) አገልግሎቱ በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የሚመለከቱ ስልጠናዎችና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲሰጣቸው ለሚጠይቅ አካል ይሰጣል።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ስልጠናዎችና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲሰጣቸው ጥያቄ የቀረበው ከግል ተቋማት በሆነ ጊዜ ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ መክፈል አለባቸው።

## 52.ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ለማውጣት ይችላል፡፡

2) አገልግሎቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎችና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 53.ተፈጻሚነት የሚኖራቸው ህጎች

1) በዚህ አዋጅ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ንብረትን የመመርመር፣ የማገድ፣ የመያዝ፣ መውረስ፣ ማስተዳደር ስነሥርዓት ወይም አለም ዓቀፍ ትብብር እንደ አስፈላጊነቱ በንብረት ማስመለስ አዋጅ ....... መሰረት ይመራል፡፡

2) የሽብር ወንጀልን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ 1176/2012 ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## 54.የዳኝነት ስልጣን

1) የአመንጭ ወንጀሉን የመዳኘት ስልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት በወንጀል የተገኘ ንብረት ህጋዊ ማስመሰል ወንጀሉንም የመዳኘት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

2) የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት ወንጀል ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡

## 55. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

1) በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 780/2005 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2) በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ እና ልማዳዊ አሠራር ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**56.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ …… ቀን ….. ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

**አባሪ አንድ**

1. በተደራጁ የወንጀለኛ ቡድኖች ውስጥ መሳተፍ እና የአሻጥር ወንጀል
2. ሽብር፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳት
3. በሰው የመነገድ እና ሰዎችን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር
4. ወሲባዊ ብዝበዛ፣የልጆች ወሲባዊ ብዝበዛን ጨምሮ
5. በናርኮቲክ መድኃኒቶች እና በሳይኮትሮፒክ ንጥረነገሮች ሕገ-ወጥ ንግድ;
6. ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር፣
7. ህገ-ወጥ ሸቀጦች ዝውውር፣ illicit trafficking in stolen and other goods
8. ሙስና እና ጉቦ፣
9. ማታለል፣
10. የመገበያያ ገንዘብን አስመስሎ መስራት፣
11. የሐሰተኞች እና ምርቶች ዘራፊነት፣
12. በአካባቢ ላይ የሚፈጸም ወንጀል፣
13. ግድያ፣ ከባድ የአካል ጉዳት፣
14. እገታ፣ ከሕግ ውጪ ይዞ ማስቀመጥ እና በመያዣነት መውሰድ፣
15. ውንብድና
16. ኮንትሮባንድ፣ (ከጉምሩክ እና ከቀረጥ ክፍያዎች እና ከቀረጥ ጋር በተያያዘም ጨምሮ)፣
17. የታክስ ወንጀል (ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስን ጨምሮ)
18. በማስገደድ መጠቀም
19. ፎርጀሪ
20. የባህር ውንብድና ወንጀል
21. ተገቢ ያልሆነ የንግድ ስራ እና የገበያ ማጭበርበር፡፡